# የሕገመንግስታዊ ፍርዶች መፅሔት

# (Journal of Constitutional Decisions)



## የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

**THE HOUSE OF THE FEDERATION OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**


**ቅፅ 1**

**ቁጥር 1**

ሐምሌ 2000

# የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያሳለፋቸው ዋና ዋና የሕገ-መንግሥት ውሳኔዎች

ይህ መፅሔት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገመንግሥት ትርጉም እና ሕገመንግሥታዊ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎችን በማጠናቀር በየዓመቱ የሚታተም ነው፡፡

**ቅፅ 1**

**ቁጥር 1**


አሳታሚ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት

ያጠናቀረው /compiled by/ መኮንን ፍሬው

ኢዲተሮች 1. ወልዱ መርኔ

2. ከበበ ታደሰ

3. ደሣለኝ ወዬሣ


**ሐምሌ 2000**

# ማውጫ

❖ መግቢያ.................................................. 1

❖ መቅድም................................................. 4

❖ የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት …………. 7

❖ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አባላት…… 13

❖ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመምረጥና መመረጥ መብት ዙሪያ ለቀረበው ሕገመንግስታዊ ጥያቄ የተሰጠ ውሳኔ ………………………….................... 14

❖ በወ/ሮ ከድጃ በሽር የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የተሰጠ ውሳኔ …………. 34

❖ በስልጤ ህዝብ የማንነት ሕገመንግስታዊ ጥያቄ ላይ የተሰጠ ውሳኔ………………………………………….. 40

## መግቢያ

ይህ መፅሔት በየዓመቱ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት የሚታተም ሲሆን ምክር ቤቱ በሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄዎች ላይ በየጊዜው የሚሰጣቸውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔዎች በማሳተም ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ1987 የኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 53 እና 61 የተቋቋመና የም/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር ለማጠናከር በወጣ አዋጅ ቁጥር 251/1993 ስልጣንና ኃላፊነቱ ተዘርዝሮ በአግባቡ ከተሠጠው ጊዜ ጀምሮ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ከምክር ቤቱ ዋና ዋና ስልጣን እና ኃላፊነቶች አንዱ ሕገመንግስቱን መተረጐም ሲሆን ም/ቤቱ በህገመንግስት ትርጉም ላይ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በጆርናል የማሳተም እና ለህዝብ የማሳወቅ ኃላፊነት ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ተጥሎበታል፡፡ በተጨማሪም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገመንግስት ትርጉም ጉዳዩች ላይ ውሳኔ የሚሰጠው በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚቀርብለት የውሳኔ አስተያየት መሰረት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በርካታ የሕገመንግስት ትርጉም አቤቱታዎችን ተቀብሎ የመረመረ ሲሆን፤ የሕገመንግስት ትርጉም እንደሚያስፈልጋቸው የሚታመ ንባቸውን አቤቱታዎች ብቻ

መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለውሳኔ እንደሚያቀርብ ይታወቃል፡፡

በዚህ መፅሔት ውስጥ የቀረቡት ውሣኔች በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል በተባሉ አቤቱታዎች ላይ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ፣ በአጣሪ ጉባኤው የሕገመንግስት ትርጉም የማያስፈልጋቸው በመሆኑ የተዘጉ በርካታ አቤቱታዎች አሉ፡፡ እነዚህ አቤቱታዎች ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ሳይቀርቡ የተዘጉ በመሆኑ በዚህ መጽሔት ያልተካተቱ ናቸው፡፡ (ለሕገመንግስት አጣሪ ጉባኤ የቀረቡ አቤቱታዎች ዝርዝር በአባሪ I ይመልከቱ)

በዚህ መጽሔት ከተካተቱት ውሳኔዎች በቀላሉ መረዳት እንደሚቻለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሣኔ አሰጣጥ ስልት ወጥ አይደለም ፡፡ በተወሰኑት ጉዳዮች ላይ የተላለፈው ውሳኔ በቃለ ጉባኤ መልክ የተቀመጠ ሲሆን በሌሎች ጉዳዬዎች ላይ ግን እንደ መደበኛ የዳኝነት ፍርድ አፃፃፍ የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ አሰራር ምንም መሠረታዊ ችግር የማያመጣ መሆኑ ቢታወቅም፣ ለወደፊቱ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔዎችን አንድ ወጥ በሆነ ስልት እንደሚሰጥ ይታመናል ፡፡ ለዚህ መጽሔት ህትመት ግን

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔዎች በአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 11 መሰረት ወደፊት ለሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ህግ ሆነው የሚያገለግሉ ስለሆነ ምንም አይነት የቅርጽም ሆነ የይዘት ለውጥ ሳይደረግባቸው እንዳሉ በዚህ መጽሔት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

# መቅድም

በ1987 ዓ.ም. በፀደቀው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 1 እንደተደነገገው የሀገራችን የመንግሥት አወቃቀር ፌዴራላዊና ዲሞክራሲያዊ ሲሆን በተለይም ለሀገራችን ሁኔታ ተስማሚ የሆነውን ሕብረብሔራዊ ፌዴራሊዝም ለመገንባትና በጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆም መንግሥትና ሕዝብ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች አድርገዋል እያደረጉም ናቸው፡፡ የፌዴራላዊ ሥርዓቱ አንዱ መገለጫ የተለያዩ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አካላትን ሥልጣንና ኃላፊነት የሚያስቀምጥ፣ ለዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ የሚያደርግ ሕገ መንግሥትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መኖሩ ነው፡፡

የምንከተለው የፌዴራል የመንግሥት አወቃቀር በመሆኑ በተለያዩ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት መካከል ባለው የሥልጣን ክፍፍል ጉዳይ ጥያቄ መነሳቱ፣ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግሥታት ሕጎች ከሕገ መንግሥቱ ጋር ቢቃረኑ ክርክር መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ታዳጊ በመሆኑ የዜጎች ሕገ መንግሥታዊ መብቶችና ነፃነቶች በመንግሥት አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው ተገቢ ያልሆነ አሠራር ቢጣሱ አቤቱታዎች መቅረባቸው የማይቀር ነው፡፡ እነዚህን ዓይነት ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄዎች የመፍታት ሥልጣን በተለያዩ የፌዴራል ሀገራት ለመደበኛ ወይም ለዚሁ ሲባል በሚቋቋሙ ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ሲሆን በእኛ ሀገር በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 62/1/ እና 83/1/ ሕገ መንግሥቱን እንዲተረጉምና ሕገ መንግሥታዊ ክርክሮችን አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲሰጥ ሥልጣን የተሰጠው ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ነው፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤትም በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ይህን ኃላፊነት ለመወጣት እስከ አሁን በዚህ አቅጣጫ በርካታ ሥራዎችን የሰራ ሲሆን ም/ቤቱ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በመታገዝ የዜጎችን፣ የብሔር ፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች የሚያስከብሩ ሕገ መንግሥታዊ ውሣኔዎችን አሳልፏል፡፡ እነዚህ ውሣኔዎች ለፌዴራል ሥርዓቱ መጠናከርና ለሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጉልህ አስተዋጽኦ ከማበርከታቸውም በላይ የምክር ቤቱን

ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/93 ዓ.ም. አንቀጽ 11/1/ እንደተደነገገው ውሣኔዎቹ ወደፊት በሚነሱ ተመሳሳይ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ የአስገዳጅነት ባህርይ ስለሚኖራቸው ማናቸውም የመንግሥት አካላትም ሆነ ዜጎች እንዲያውቋቸው ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከላይ ባለው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ መሠረት ውሣኔዎቹን ሕዝብ እንዲያውቃቸው ለዚሁ ዓላማ ምክር ቤቱ በሚያዘጋጀው ልዩ መጽሔት ታትመው ይወጣሉ፡፡

ይህን ሕጋዊ አካሄድ በመከተል እነሆ ምክር ቤቱ በሦስት ጉዳዮች ላይ የሰጣቸውን ሕገ መንግሥታዊ ውሣኔዎች የያዘ የመጀመሪያ ቅጽ በጆርናል መልክ ታትሞ እንዲወጣ አድርጓል፡፡ ወደፊትም በተመሳሳይ መልኩ ይቀጥላል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ውሣኔዎች 1ኛ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት በሕጉ በተቀመጠው መሠረት ተመሳሳይ ጉዳይ ቢያጋጥማቸው እንደ ሕግ እንደሚጠቀሙባቸው 2ኛ ዜጎችም ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸውንና ነፃነቶቻቸውን የሚያስከብርላቸው ሕገ መንግሥታዊ አካል መኖሩን ግንዛቤ ወስደው መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩ በማገዝ በኩል አንድ እርምጃ ወደፊት ይወስዳሉ የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡

**ደግፌ ቡላ ዋቅጅራ**
**የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ**

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት

| ተራ ቁጥር | የተወካዩ ስም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 1 | የተከበሩ አቶ መሀመድ ኢሳቅ | ሶማሌ |
| 2 | የተከበሩ ዶ/ር መሐመድ ሰርሀዬ | ሶማሌ |
| 3 | የተከበሩ አቶ አወል ወገሪስ | አፋር |
| 4 | የተከበሩ አቶ እስማኤል አሊሲሮ | " |
| 5 | የተከበሩ አቶ አብዱልዋሲዕ ዩሱፍ | ሐረሪ |
| 6 | የተከበሩ አቶ ሐሰን ኢብራሂም | ሶማሌ |
| 7 | የተከበሩ አቶ ዳውድ መሀመድ አሊ | " |
| 8 | የተከበሩ አቶ ሰይድ የሱፍ | አማራ |
| 9 | የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ደመቀ | " |
| 10 | የተከበሩ ወ/ሮ ሙሉነሽ ተስፋዬ | ደቡብ |
| 11 | የተከበሩ አቶ ባረካ ከበረኮሮ | " |
| 12 | የተከበሩ አቶ ባዘዘው ጫኔ | አማራ |
| 13 | የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው | " |
| 14 | የተከበሩ አቶ አልቶ ባሎ | ደቡብ |

| | | |
|---|---|---|
| 15 | የተከበሩ አቶ ዶሳ ማዳ | “ |
| 16 | የተከበሩ ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም | “ |
| 17 | የተከበሩ አቶ ወዶ አጦ | “ |
| 18 | የተከበሩ ወ/ሮ አማረች በካሎ | “ |

| ተራ ቁጥር | የተወካዩ ስም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 19 | የተከበሩ ወ/ት ፈዲላ አደም | ደቡብ |
| 20 | የተከበሩ አቶ ቢኒያም ባቡ | “ |
| 21 | የተከበሩ ወ/ሮ ታደለች ከበደ | “ |
| 22 | የተከበሩ አቶ ኑረዲን ሃሰን | “ |
| 23 | የተከበሩ አቶ አያሌው ጐበዜ | አማራ |
| 24 | የተከበሩ ዶ/ር ምስራቅ መኮንን | “ |
| 25 | የተከበሩ ዶ/ር መሐመድ ሐሰን | ኦሮሚያ |
| 26 | የተከበሩ አቶ አባዱላ ገመዳ | “ |
| 27 | የተከበሩ አቶ ጁኔይድ ሣዶ | “ |
| 28 | የተከበሩ ወ/ሮ ፎዚያ አሚን | “ |
| 29 | የተከበሩ አቶ ፍቅሩ ኛካል | ደቡብ |
| 30 | የተከበሩ አቶ ባርጎዴ ባንጫ | “ |
| 31 | የተከበሩ አቶ ጌታቸው አምባዬ | አማራ |
| 32 | የተከበሩ አቶ ዮሐንስ ጌታሁን | “ |
| 33 | የተከበሩ አቶ ደግፌ ቡላ | ኦሮሚያ |
| 34 | የተከበሩ አቶ ለማ መገርሣ | “ |

| | | |
|---|---|---|
| 35 | የተከበሩ አቶ ፀጋዬ ማሞ | ደቡብ |
| 36 | የተከበሩ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ | “ |
| 37 | የተከበሩ አቶ ፀጋዬ በርሄ | ትግራይ |
| 38 | የተከበሩ አቶ አባይ ወልዱ | “ |

| ተራ ቁጥር | የተወካዩ ስም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 39 | የተከበሩ አቶ ወርቅነህ መኮንን | አማራ |
| 40 | የተከበሩ አቶ ጌታቸው ጀንበር | “ |
| 41 | የተከበሩ አቶ አለሙ ስሜ | ኦሮሚያ |
| 42 | የተከበሩ አቶ አብዱልአዚዝ መሐመድ | “ |
| 43 | የተከበሩ አቶ ደሴ ዳልኬ | ደቡብ |
| 44 | የተከበሩ አቶ ሬድዋን ሁሴን | “ |
| 45 | የተከበሩ አቶ ብርሃነ ኃይለስላሴ | ትግራይ |
| 46 | የተከበሩ ወ/ሮ ሮማን ገ/ስላሴ | “ |
| 47 | የተከበሩ አቶ አምባቸው አባተ | አማራ |
| 48 | የተከበሩ አቶ ዮሐንስ ቧያለው | “ |
| 49 | የተከበሩ ወ/ሮ አቲካ መሐመድ | ኦሮምያ |
| 50 | የተከበሩ ወ/ሮ ሩቅያ ኡኬ | “ |
| 51 | የተከበሩ ወ/ሮ ደስታ ዱኬ | ደቡብ |
| 52 | የተከበሩ አቶ አቡቶ አኒቶ | “ |
| 53 | የተከበሩ አቶ ቹርጳላ ባርኮሩቡኔ | “ |
| 54 | የተከበሩ ወ/ሮ ደሃብ ደበሳይ | ትግራይ |

| | | |
|---|---|---|
| 55 | የተከበሩ ወ/ሮ ሰርካለም እስከዚያ | አማራ |
| 56 | የተከበሩ አቶ አይቸው ከበደ | " |
| 57 | የተከበሩ አቶ ቀነአ ያደታ | ኦሮሚያ |
| 58 | የተከበሩ አቶ ሙስጠፋ | " |

| ተራ ቁጥር | የተወካዩ ስም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 59 | የተከበሩ አቶ ጉናስና ባሻማጂ | ደቡብ |
| 60 | የተከበሩ አቶ አርካይዳ ኦራይታ | " |
| 61 | የተከበሩ አቶ አስራቱ ኮነቭ | " |
| 62 | የተከበሩ አቶ ሙሉጌታ ፈጠነ | " |
| 63 | የተከበሩ አቶ መላኩ አለኸኝ | አማራ |
| 64 | የተከበሩ አቶ አሰፋ በላይ | " |
| 65 | የተከበሩ አቶ ጀማል ኡስማን | ኦሮሚያ |
| 66 | የተከበሩ አቶ ተክሌ ዴሬሣ | " |
| 67 | የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ሞርካቲ | ደቡብ |
| 68 | የተከበሩ አቶ አዳነ ገበየሁ | " |
| 69 | የተከበሩ ወ/ሮ ሙለእመቤት ዳና | " |
| 70 | የተከበሩ አቶ አዴሎ መሀሪ | " |
| 71 | የተከበሩ አቶ አለባቸው ንጉሴ | አማራ |
| 72 | የተከበሩ አቶ ሁሴን ገልገሎ | ኦሮሚያ |
| 73 | የተከበሩ አቶ መሐመድ ጅሎ | " |
| 74 | የተከበሩ ወ/ሮ በቀለች ፈዬ | " |

| | | |
|---|---|---|
| 75 | የተከበሩ ወ/ሮ ገነት ወልዴ | ደቡብ |
| 76 | የተከበሩ አቶ ታደሰ ሴላ | “ |
| 77 | የተከበሩ ወ/ሮ አበራሽ አምዛዬ | “ |
| 78 | የተከበሩ ሲ/ር ዘሪቱ ጋሼ | “ |

| ተራ ቁጥር | የተወካዩ ስም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 79 | የተከበሩ አቶ መሐመድ አብዶሽ | ኦሮሚያ |
| 80 | የተከበሩ ወ/ሮ ሂርጴ ሙለታ | “ |
| 81 | የተከበሩ አቶ ጉማቸው ኩሴ | ደቡብ |
| 82 | የተከበሩ አቶ ዳንኤል ሳሙኤል | “ |
| 83 | የተከበሩ ወ/ሮ ፋናዬ አበበ | “ |
| 84 | የተከበሩ አቶ ያዕቆብ ያላ | “ |
| 85 | የተከበሩ አቶ ደቻሣ አለማየሁ | “ |
| 86 | የተከበሩ አቶ ሲጐለኝ ሰማጃሮ | “ |
| 87 | የተከበሩ ዶ/ር ወልደሩፋኤል | ትግራይ |
| 88 | የተከበሩ አቶ ኡሞድ ኡቦንግ | ጋምቤላ |
| 89 | የተከበሩ አቶ ያረጋል አይሸሹም | ቤንሻንጉል |
| 90 | የተከበሩ አቶ ጓነር የር | ጋምቤላ |
| 91 | የተከበሩ አቶ ሰይፈዲን ሀሩን | ቤንሻንጉል |
| 92 | የተከበሩ አቶ ወይናቶ አበራ | ጋምቤላ |
| 93 | የተከበሩ አቶ ጁል ላንጋል | “ |
| 94 | የተከበሩ አቶ በዛብህ አለም | ቤንሻንጉል |

| | | |
|---|---|---|
| **95** | **የተከበሩ አቶ አቶም መሀመድ** | " |
| **96** | **የተከበሩ አቶ ረመዳን አሸናፊ** | " |
| **97** | **የተከበሩ ወ/ሮ አርቲ ማያ** | " |

| ተራ ቁጥር | የተወካዩ ስም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 98 | የተከበሩ አቶ ርስቱ ይርዳው | ደቡብ |
| 99 | የተከበሩ አቶ ሙሉጌታ ሀሎ | " |
| 100 | የተከበሩ አቶ ዳንኤል ደምሴ | " |
| 101 | የተከበሩ አቶ አደማ ትንጳዬ | " |
| 102 | የተከበሩ አቶ ጌታቸው ቶርጫ | " |
| 103 | የተከበሩ አቶ ሙደር ሰማን | " |
| 104 | የተከበሩ አቶ ባሕሩ አኩ | " |
| 105 | የተከበሩ አቶ አማረ ሀቱዬ | " |
| 106 | የተከበሩ አቶ መሸሻ ደሳለኝ | " |
| 107 | የተከበሩ አቶ ብርሃኑ ጦፋ | " |
| 108 | የተከበሩ አቶ ካይዳኪ ገዛኸኝ | " |
| 109 | የተከበሩ አቶ ክፍሌ ፎንቃሞ | " |
| 110 | የተከበሩ አቶ አበበ አቲቻ | " |
| 111 | የተከበሩ አቶ ጐርፉ ሲጊዶ | " |
| 112 | የተከበሩ አቶ አባይነህ ሂሎ | " |
| 113 | የተከበሩ ወ/ሮ ቦና ባላንታ | " |
| 114 | የተከበሩ ወ/ሮ አይካ ባዳኔ | " |
| 115 | የተከበሩ አቶ ሣዲቃ ሻይጫ | " |
| 116 | የተከበሩ አቶ አፍራ ጉርሣ | " |
| 117 | የተከበሩ አቶ ላሊ ቢዋ | " |
| 118 | የተከበሩ አቶ ገነሞ ዋዶ | ደቡብ |
| 119 | የተከበሩ አቶ ኮሊ ጉለይ | " |
| 120 | የተከበሩ አቶ ኤካፊል ኢቱር | " |

# የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አባላት

1. ክቡር አቶ ከማል በድሪ ………………… ሰብሳቢ
2. ክቡር አቶ መንበረ ፀኃይ ታደሰ ……. ም/ሰብሳቢ
3. የተከበሩ አቶ ደግፌ ቡላ ……….………… አባል
4. የተከበሩ አቶ አባይ ወልዱ ……………..…… አባል
5. የተከበሩ አቶ ሀሰን ኢብራሂም ………..…. አባል
6. የተከበሩ አቶ ኩማ ደመቅሳ ……..……… አባል
7. ክቡር ዶ/ር ፋሲል ናሆም ………….……. አባል
8. ክቡር ዶ/ር ሀሺም ቶፊቅ ……………… አባል
9. ክቡር አቶ ጌታሁን ካሳ …………………. አባል
10. ክቡር አቶ ሙሉጌታ አያሌው ….……… አባል
11. ክቡር አቶ በየነ ቢልቱ …………………… አባል

# ክፍል አንድ

## በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመምረጥና መመረጥ መብት ዙሪያ ለቀረበው ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ በፌድሬሽን ም/ቤት መጋቢት 5 ቀን 1995 ዓ.ም. የተሰጠ ውሳኔ

### I. ፍሬ ነገር

የቀረበው አቤቱታ ሰፋ ያለና በርካታ አስተዳደራዊ ጥያቄዎችን ያካተተ ሆኖ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በስልጣኑ ክልል ሊታይ በሚገባው የመምረጥና መመረጥ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ሌሎች ጥያቄዎች በክልሉና በሌሎች ሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚመለሱ ስለሆነ ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠበት ጥያቄ ፍሬ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

#### ሀ. በመምረጥና መመረጥ ዙሪያ የቀረበ የአቤቱታ ጥያቄ

የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የትግራይና ሌሎች ብሔሮች ተወላጆች ዜጎች በ1992 ዓ.ም በመላው ሀገሪቱ በተደረገው ሕዝባዊ ምርጫ ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት ለመወዳደር በአሶሳና በባምቢሲ የምርጫ ክልል ለመሳተፍ እጩ ተወዳዳሪዎች ሲያቀርቡ በክልሉ ከሚገኙ አምስቱ ብሔሮች ማለትም የበርታ፣ የጉሙዝ፣ የሽናሻ፣ የኮሞና ማኦ ብሔረሰቦች ፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የበርታ

ብሔር የፖለቲካ ድርጅት አመራሮች በስተቀር በሌሎች 4ቱ የተደገፈ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በዕጩ ተወዳዳሪዎች ከአምስቱ ብሔር አንዱ የሆነውን የበርታ ብሔረሰብ ቋንቋን መናገር ስማይችሉ ከተወዳዳሪነት እንዲሰረዙ የበርታ ፖለቲካ ድርጅት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቤቱታ አቀረበ፡፡ የምርጫ ቦርድም እጩ ተወዳዳሪዎች የበርታ ብሔረሰብ ቋንቋን መናገር አይችሉም በማለት ከምርጫው እንዲሰረዙ ወሰነ፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት በግልጽ እንደተደነገገው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቀለም፣ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከትና አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት በቀጥታና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካይነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ እንዲሁም በቋንቋው የመናገር ፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና ማስፋፋት እንዲሁም በሰፈረበት መልክዓምድር ራሱን የሚያስተዳድበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በየደረጃው በሚገኙ አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት እንዳለው ያሳረዳል በማለት የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የትግራይና የሌሎች ብሔሮች ተወካይ ነን የሚሉ አቤት ባዮች

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመምረጥና የመመረጥ መብት ሕገመንግስታዊ መብት መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ፍትሐዊ ምላሽ ሊሰጠን ሲገባ መብታችንን በሚያፍንና በብሔራዊ ማንነታችን እንዳንኮራ በሚያደረግ መልኩ ያለአግባብ ከምርጫ እንድንታገድ ማድረጉ ከዓለም አቀፍም ሕግ ሆነ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት መርሆዎ አንፃር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 9 መሰረት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ ይሻርልን በማለት በ27/6/92 አቤቱታ ለፌዴረሽን ም/ቤት አቅርበዋል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤትም በቀረበው አቤቱታ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 62/1 በተሰጠው ህገመግስታዊ ጉዳዮች የመተርጎም ስልጣን መሰረት በሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 82 በተቋቋመውና በአንቀጽ 84 ስልጣንና ተግባሩ ተለይቶ ለተሰጠው የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብለት መርቷል፡፡

## ለ. የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው የውሳኔ ሃሳብ

የአጣሪ ጉባኤው ሰኔ 28 ቀን 1992 ዓ.ም ተሰብስቦ በም/ቤቱ በተመራ ጉዳይ ላይ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ሁለት ጭብጦች ለይቶ በማስቀመጥ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል፡፡

ለምርጫ ውድድር የሚቀርቡ እጩዎች የሚወዳደሩበትን ብሔራዊ ክልል ቋንቋ ማወቅን በቅድመ ሁኔታነት የሚደነግገው የምርጫ አዋጅ አንቀጽ 38/1/ለ ከህገመ ንግስቱ ጋር ይቃረናል ወይስ አይቃረንም?
በአዋጅ ቁጥር 111/87 መሰረት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያስተላለፈው ውሳኔ ህገመንግስታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡ ጉባኤውም በነዚህ ጭብጦች ላይ ውይይት ካካሄደ በኃላ ቀጥሎ የተመለከተውን የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

### የአብላጫው የውሳኔ ሃሳብ

የህገመንግስቱ አንቀጽ 38 ዜጎች ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው በቀጥታና በነፃነት በመረጧቸው ተወካዮቻቸው በኩል በህዝብ አስተዳደር ጉዳይ ላይ የመሳተፍ መብት ያላቸው መሆኑን ሲደነግግ በተወዳ

ዳሪዎች መካከል ደግሞ የቀለም፣ የዘር፣ የብሔር ብሔረሰብ፣ የጾታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም የሌላ አመለካከት ልዩነት ሳይደረግባቸው የመወዳደር መብት ያላቸው መሆኑን ያመለክታል በአንፃሩ ደግሞ የምርጫ ህጉ በአንቀጽ 38/1/ለ ስር ማንኛውም በእጩነት የሚቀርብ ተወዳዳሪ የሚወዳደርበትን የብሄራዊ ክልል ቋንቋ ማወቅ ያለበት መሆኑን ደንግጓል፡፡

የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 111/87 አንቀጽ 38/1/ለ የአንድን ሰው በእጩ ተወዳዳሪነት መቅረብ ቅድመ ሁኔታ አድርጎ ማስቀመጡ በህገመንግስቱ ከተረጋገጠው የመምረጥና የመመረጥ መብት አንቀጽ ሲታይ ከህገመንግስቱ ድንጋጌ ጋር ተጣጥሞ የሚካሄድ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም ህገ መንግስቱ ዜጎች በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት በአገራቸው ጉዳይ ላይ እንዲሳተፉ ለማስቻል የመምረጥና የመመረጥ መብታቸውን እንዲጠቀሙ በግልጽ የደነገገ ሲሆን አዋጁ ግን ይህን መብት በመጠቀም ቋንቋን እንደመስፈርት ወስዶ የአንድን ክልል ብሄራዊ ቋንቋ የማያውቁ ነዋሪዎች ይህን መብታቸውን በመገደቡ ነው፡፡ ስለሆነም የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 111/87 አንቀጽ 38/1/ለ ከህገመንግስቱ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል ሲል ወስኗል፡፡

እነዚህን ጭብጦች መሰረት አድርጎ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገመንግስት አጣሪ ጉባኤ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ዜጎች ምንም አይነት ልዮነት ሳይደረግባቸው የመመረጥና የመምረጥ መብታቸው መጠበቅ እንዳለበት ተደንግጎ እያለ በምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 111/87 በአንቀጽ 38/1/ለ ስር ማንኛውም በእጩነት የሚቀርብ ተወዳዳሪ የሚወዳደርበትን የብሔራዊ ክልል ቋንቋ ማወቅ አለበት በሚል የተደነገገው የአንድን ክልል ቋንቋ የማያውቁ ነዋሪዎችን መብት የሚገድብ በመሆኑ የምርጫ ሕግ አዋጅ ከሕገመንግስቱ ጋር ይቃረናል፡፡ የህገመንግስት ትርጉም ያሻዋል፣ /ያስነሳል/ የሚል ነው፡፡

## የአናሳው የውሳኔ ሃሳብ

አዋጁ ከሕገመንግስቱ ጋር የማይቃረን መሆኑን ለማሳየት የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 111/87 አቀንጽ 38/1/ለ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት አወቃቀር ጋር ተያይዞ እያንዳንዱ ክልልና ሕዝብ ራስን በራስ ማስተዳደር ከሚለው መርህ ጋር በተጣጣመ መልኩ ተመራጩ የሚያገለግለበትን ሕዝብ ቋንቋ በማወቅ እንዲመራው የሚል መነሻ የያዘ እንጂ በማንም ዜጋ ላይ በልዩ ሁኔታ የመመረጥና የመምረጥ መብትን ለመጋፋት የፌዴራሉን ሕገመንግስት አንቀጽ 38 ለመቃረን የተቀመጠ እንዳልሆነ አስፍረዋል፡፡

## ሐ. <u>የሙያ አስታያየት</u>

የፌዴሬሽን ም/ቤትም ከአጣሪ ጉባኤው የቀረቡለትን የውሳኔ ሃሳብ በ1993 ዓ.ም 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በበቂ ሁኔታ ከመከረበት በኃላ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከር ስልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 8 መሰረት ምክር ቤቱ ተጨማሪ የባለሙያዎች አስተያየት በማሰባሰብ ለምክር ቤቱ የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመራለት ሲሆን የህግ ቋሚ ኮሚቴም በጉዳይ ላይ የተለያዩ የሕግ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡

# <u>ትንተና</u>

## <u>ጭብጦች</u>

1. ከባለጉዳዮች የቀረበውን አቤቱታ፣ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት ግምት ውስጥ በማስገባት የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ለመወሰን፤

2. አዋጅ ቁጥር 111/87 አንቀጽ 38/1/ለ ቋንቋ አንድ ሰው እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ ከሚያቡቁ መመዘኛዎች አንዱ

አድርጎ መደንገጉ ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 38/1/ለ ጋር ይቃረናል ወይስ አይቃረንም?

3. የምርጫ ቦርድ ውሳኔ ህገመንግስታዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች መርምሮ ውሳኔ ላይ መድረስ ይጠይቃል፡፡ እነዚህን ጭብጦች ለመወሰን የህገመንግስቱን አላማዎችና ግቦች፣ የአገራችንን የመንግስት አወቃቀርና የስልጣን መሰረት፣ መሰረታዊ የግለሰብና የብሔር ብሔረሰቦችን መብቶችና ነፃነቶችን በእኩልነት መተግበርን፣ እንደ አገርና እንደ ህዝብ ያሳለፍናቸውን የታሪክ ተሞክሮዎች እና መታረም ያለባቸውን ታሪካዊ የተዛባ ግንኙነቶችን በአጠቃላይ የሕገመንግስት የበላይነትን ከግምት ማስገባት የመፍትሔው መነሻና ማእቀፍ አድርገን ጉዳዩን ማጤን ይገባል፡፡

## የሕገመንግስት የበላይነት

ህገ መንግስቱ የዜጎችና የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መሰረታዊ መብቶች የተደነገጉበት፣ የመንግስት አወቃቀር ከነስልጣንና ኃላፊነታቸው እንዲሁም የአሰራር ስርአታቸው የሰፈረበት፣ አገሪቱ የምትመራበት መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ፖሊሲዎች የተቀመሩበት ሲሆን የህዝቦች የወደፊት ራእይ ቃል ኪዳን ማሰሪያ ነው፡፡ በህገመንግስቱ አንቀጽ 9 እንደተደነገገው ህገመንግስቱ የአገሪቱ የበላይ ህግ እንደመሆኑ መጠን ማንኛቸውም ህግ፣ ልማዳዊ

አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከህገመንግስቱ ጋር መጣጣም እንዳለበት የግድ ይላል፡፡ ነገር ግን ማንኛቸውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከህገመንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9 መሰረት ህገመንግስቱን ተርጉሞ ህጉ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

## የመንግስት አወቃቀርና የህዝብ ሉአላዊነት

የህገመንግስታችን አንቀጽ 1 ና 8 ፌዴራላዊና ዴሞክራሳዊ የመንግስት አወቃቀርና የሕዝብ ሉአላዊነትን ይደነግጋል፡፡ ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ የመንግስት አወቃቀርና የህዝብ ሉአላዊነት ምን ማለት እንደሆነ እና መገለጫቸውም በህገመንግስቱ የተለያዩ ምዕራፎችና አንቀጾች ስር በግለፅና በዝርዝር የሰፈሩ ሲሆን አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ያላቸውን ትስስርና አግባብነት በአጭሩ እናብራራለን፡፡

ፌደራላዊ የመንግስት አወቃቀር ስንል ስልጣን በአንድ ላይ ከማማከል ይልቅ በፌዴራልና በክልል ከፋፍሎ አገሪቱን በአጠቃላይ የሚመለከቱ ጉዳዮች በፌዴራል መንግስት እንዲሁም የክልሎች የውስጥ ጉዳዮች በክልሎች በራሳቸው የሚወሰንበት የፖለቲካ ስርአት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት በክልሎች የተዋቀረ ሲሆን

በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነት እና ፍቃድ ላይ መሰረት ባደረገ አወቃቀር 9 ክልሎች አሉት፡፡ ይህ ማለት ግን በእያንዳንዱ ክልል የሚኖረው ህዝብ ሁሉ አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገርና አንድ አይነት ባህል አለው ማለት አይደለም፡፡ ይህ አይነት የመንግስት አወቃቀር የተመረጠው በአገራችን ኢትዮጵያ ደም ሲያፋስስና ለውድመት የዳረገንን የብሔሮችና ብሔረሰቦች እራስን በራስ የማስተዳደር፣ በቋንቋ የመጠቀም፣ የመማርና ባህልንና ታሪክን የማዳበርና የመንከባከብ መብቶች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ስንል በዋነኛነት ከላይ እስከታች ያሉ የፌዴራሉም ሆነ የክልል የመንግስት አካላት ሁሉ አቀፍ፣ ፍትሀዊ፣ ነጻ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተና ድምጽ በሚስጢር በሚሰጥበት ስነ ስርአት በሚካሄድ ምርጫ በሕዝብ የሚመረጡበት እና የግለሰቦችና የቡድኖች ሰብአዊና ዴሞክሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ የሚከበሩበት ስርአት ነው፡፡ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆናቸው በህገመንግስቱ አንቀጽ 8 ሰፍሯል፡፡ በመሆኑም ማናቸውም ስልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ ነው፡፡ ሕዝብ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት ሆነ ማለት በተወካዮቹ አማካኝነት የመጨረሻውን የፖለቲካ ስልጣን ጨበጠ ማለት ነው፡፡ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት በሆነበት ዲሞክሲያዊ ስርአት ደግሞ የዜጎች የመምረጥና የመመረጥ መብት ሙሉ  በሙሉ የተጠበቀ ነው፡፡ የመምረጥና የመመረጥ መብት አይነተኛ ግቡ ዜጎች መሪዎቻቸውንና

አስተዳዳሪዎቻቸውን ራሳቸው እንዲመርጡና እንዲሽሩ ለማስቻል ነው፡፡ ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው ሲከበር በሕዝብ አስተዳደር ማለትም በፖለቲካ ጉዳይ ሙሉና ቀጥተኛ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡ የዚህ መብት መረጋገጥ ለምንገነባው ዲሞክራሲያዊ ስርአት መረጋገጥ አማራጭ የሌለው ዋስትናን ይሰጣል፡፡ በመሆኑም በህገመንግስታችን አንቀጽ 38 መሰረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ የግል አመለካከቱና እምነቱ ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው፡፡

## የግለሰቦችንና የብሔር ብሔረሰቦችን የእኩልነት መብቶች

## በእኩልነት ስለመተግበር

የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ እና ሕዝቦች እንድሁም የዜጐች /የግለሰቦች/ የእኩልነት መብቶች በህገመንግስታችን በአንቀጽ 25 እና በአንቀጽ 39 በንኡስ አንቀጽ 2 ና 3 ላይ ሰፍረው እናገኛቸዋለን፡፡

በሕገመንግሰቱ አንቀጽ 25 መሰረት ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፣ በመካከላቸውም ማንኛቸውም አይነት በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም

ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ ስለሆነም እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በሁሉም ደረጃ የሚገኝ የመንግስት አካል ማንኛውንም ሕግ በሚያወጣበት፣ በሚተረጉምበትና በስራ ላይ በሚያውለበት ጊዜ በሰዎች መካከል ከላይ በጠቀስናቸው ማንኛቸውም አይነት ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግ ሁሉንም በእኩል አይን የሚያይ እና ለሁሉም በእኩልነት ዋስትናና አለኝታ መሆኑን ማስመስከርና ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የሕገ መንግስታችን አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2 ና 3 ሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀምና ቋንቋን የማዳበር፣ ባህላቸውን የመግለፅና የማዳበር፣ የማስፋፋት፣ ታሪካቸውን የመንከባከብ፣ ራሳቸውን የማስተዳደር እና በጋራ ተቋሞች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በእኩልነት የመወከል መብቶች እንዳለቸው ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ደግሞ የማንነታቸው መግለጫ የሆነ የራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና፣ ታሪክ አላቸው በመሆኑም የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ እኩል የህግ እውቅናና ጥበቃ አለው ማለት ነው፡፡

ከላይ ከጠቀስናቸው ሁለት ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው በዜጎችም ሆነ በብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መካከል ልዩነትና አድሎ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም የግለሰቦችና የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

የተሳሰሩ፣ የማይነጣጠሉና እኩል እንደሆኑ፣ አንዱ ከሌላ የማይበልጥ ወይም የማያንስ እንደሆነ እንዲሁም አንዱ ለሌላው ሲባል መብቱና ነጻነቱ እንደማይሸራረፍና ገደብ እንደማይጣልበት ነው፡፡ ስለሆነም ተጣጥመው በእኩልነት መተግበር እንዳለባቸው ነው ህገመንግስታችን የሚያስቀምጠው፡፡ ከዚህ አንጻር የዜጎች የመምረጥ መብትን አስመልክቶ የቀረበው ጥያቄ ከብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ባህላቸውን የማዳበር፣ እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ጋር ካለምንም እድልዎና ልዩነት በሕገመንግስቱ መሰረት እንዴት በእኩልነት ተጣጥመው መተርጎምና መተግበር እንዳለባቸው ለማየት እንሞክራለን፡፡

ሕገመንግስታችን ሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብት አላቸው ሲል አንዱ የሌላውን ቋንቋ ማወቅና መማር የለባቸውም ማለት እንዳልሆነ ትኩረት ሊሰጠውና ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ አሁን በአለምም ሆነ በአገር ደረጃ እየተጠናከረና ይበልጥ እየጎለበተ በመሄድ ላይ ካለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነትና ትስስር አንጻር የአለምም ሆነ የአገራችን ህዝቦች በነጻ ፍላጎታቸው በተለያየ ደረጃ እርስ በርሳቸው የሚያገናኛቸው የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች በሂደት የማዳበራቸው ሁኔታ አይቀሬ ነው፡፡ ይህን እውነታ በመገንዘብ ነው ህገመንግስታችን በአንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ 2 ና 3 ላይ አማርኛ የፌዴራሉ መንግስት የስራ

ቋንቋ እንደሆነና ክልሎች ደግሞ የየራሳቸውን የስራ ቋንቋ በሕግ እንደሚወስኑ የደነገገው፡፡

ይህ ድንጋጌ በአንድ በኩል ዜጎች የጋራ ጉዳያቸውን በጋራ በሚያግባባቸው ቋንቋ በራሳቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት አስተዳደራዊ የእለት ተእለት ኑሮአቸውን እንዲያከናውኑ በሌላ በኩል ደግሞ ብሔር ብሔረሰቦች በተለያየ የአስተዳደር እርከን እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ፣ በቋንቋቸው እንዲማሩና እንዲሰሩ ባህላቸውንና ታሪካቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡

የሕዝብ ወይም የብሔርና ብሔረሰቦች ተወካዮች በጋራ መክረው በነጻ ፍላጎታቸው የፌዴራሉን መንግስት ሆነ የየክልሉን የስራ ቋንቋ ሲወስኑ በዜጎች ወይም በብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መካከል ልዩነትን፣ አድሎንና መገለልን ለመፍጠር ወይም የአንዱን ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ቋንቋ የሚናገረውና የሚግባባበት በመሆኑ ለጋራ ጠቃሚታ ሲባል ለሁሉም በእኩልነት እንዲያገለግል በማሰብ ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ቋንቋ አብዛኛውን ህዝብ ያግባባል በሚል የስራ ቋንቋ ሆኖ ሲመረጥ ሌሎች ቋንቋዎችን ማዳበር ወይም በተለያየ ደረጃ መጠቀም አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ እንዲሁም እጩ ተወዳዳሪዎችን የመምረጥና ያለመምረጥ መብት የመራጩ ህዝብ ቢሆንም እጩ ተወዳዳሪዎች የራሳቸውን ወይም የሚወክሉትን የፖለቲካ ፖርቲ መርሀ-ግብር ለመራጩ ህዝብ ለማስተዋወቅና ለማስረዳት ከተመረጡ በኋላም

አባል በሆኑበት ምክር ቤት ውስጥ የወከሉትን ሕዝብ ሀሳብ፣ ፍላጎት፣ ብሶት በትክክል እና እንደተፈለገው ለመግለጽ በዛ ላይ ለመምከር የተመረጡበትን ምክር ቤት የስራ ቋንቋ ማወቅ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ የመራጩን ሕዝብ መብትና ጥቅም በተሟላ መልኩ ለማስጠበቅ የጎላ ጠቄሜታ እንዳለው ግልፅ ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ሰው እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመመዝገብና ለመመረጥ የሚወዳደርበት ምክር ቤት የጋራ መግባቢያ የሆነውን የስራ ቋንቋ ማወቅ እንደ አንድ መመዘኛ በሕግ መቀመጡ በማናቸውም መለኪያ ቢታይ በዜጎች መካከል ልዩነት የሚፈጥርና የዜጎችን የመመረጥ መብት የሚገድብ፣ የሚሸራርፍ ወይም የሚያሳጣ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 38 ጋር አይጋጭም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አንድ ሰው የስራ ቋንቋውን እስከቻለ ድረስ በየደረጃው የጋራ ጉዳዮች በጋራ በሚመከርበት ም/ቤት ለመመረጥ በእጩነት መቅረቡ ወይም መመረጡ በማናቸውም መልኩ የማንኛውንም ብሔረሰብ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሚገድብ ወይም የሚሸራርፍ ወይም የሚያሳጣ አይደለም፡፡ የመምረጥና የመመረጥ መብትን የሚደነግገው የህገመንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚከለክለው ቋንቋን ለመመረጥ እንደመስፈርት ማስቀመጥን ሳይሆን በቋንቋ ምክንያት በዜጎች መካከል ልዩነትና አድሎ በመፍጠር የዜጎች የመምረጥና መመረጥ መብትን መገደብ፣ መሸራረፍ ወይም ማሳጣትን ነው፡፡ እንዲሁም የእኩልነት መብትን የሚደነግገው አንቀጽ 25 በተመሳሳይ ሁኔታ

የሚከለክለው ቋንቋን ጨምሮ በብሔር ብሔረሰብ ማንነትና ሌሎች በአንቀጹ በተደነገጉት ሁኔታዎች በዜጎች መሠረታዊና ሰብአዊ መብቶች ማንኛቸውም አይነት አድሎ እና ልዩነት ማድረግ እንደማይቻል ነው፡፡

እነዚህ የግለሰቦችና የብሔር ብሔረሰቦች የእኩልነት መብቶች በእኩልነት በጋራ መከበራቸው በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በሕግ የበላይነት እና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድ ጠንካራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ የመገንባቱን ህገመንግስታዊ አላማ ስኬታማ ለማድረግ መሰረታዊና ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት ምክንያቶች በመነሳት የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/87 አንቀጽ 38/1/ለ ቋንቋ ለመመረጥ ከሚያበቁ መመዘኛዎች አንዱ አድርጎ መደንገጉ በራሱ የሕገመንግስቱን አንቀጽ 38 ይቃረናል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡

ስለሆነም ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ አንድ ሰው ለእጩ ተወዳዳሪነት ለመመዝገብ እና ለመመረጥ የሚወዳደርበትን ምክር ቤት የስራ ቋንቋ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ የምርጫ ሕግ ቁጥር 111/87 አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ለ የተቀመጠው የቋንቋ መስፈርት ለመመረጥ የሚወዳደርበትን ምክር ቤት የስራ ቋንቋ ማወቅ ለመመረጥ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን፣ የብሔራዊ ክልሉን ቋንቋ ማወቅ ከሚለው አንቀጽ 38/1/ለ ጋር ተደጋጋፊ እንጂ አንዱ አንዱን የሚቃረን አድርጎ መውሰድ ትክክል ስላልሆነ

የሚመከታቸው አካላት በዚሁ መልክ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

የምርጫ ቦርድ በምርጫ አዋጅ ቁጥር 111/87 አንቀጽ 38 በንዑስ አንቀጽ 1/ለ የተደነገገውን የብሔራዊ ክልል ቋንቋ ማወቅ ማለት በክልሉ የሚገኙ የነባር ብሔር፣ ብሔረሰቦች ቋንቋ ማወቅ ነው በማለት በ1992 በመላው ሀገሪቱ በተደረገው ህዝባዊ ምርጫ ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ለመመረጥ የቀረቡ እጩ ተወዳዳሪዎች ከነባር ብሔር፣ ብሔረሰቦች ቋንቋ አንዱ የሆነውን የበርታ ቋንቋ አታውቁም በማለት ከምርጫው እንዲሰረዙ የሰጠው ውሳኔ ህገመንግስቱን እንደሚቃረን ለማየት እንሞክራለን፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ (የበርታ፣ የጉሙዝ፣ የሽናሻ፣ የኮሞና ማኦ) ብሔረሰቦች በዋናነት እንዲሁም ሌሎች የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የትግራይ፣ የአገው ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚኖሩበት ክልል ነው፡፡ በክልሉ የሚኖሩትን ሕዝቦች በአብዛኛው በጋራ የሚያግባባና በክልሉ ምክር ቤት በህዝቦች ነፃ ፍላጎት የክልሉ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን የመረጡት አማርኛ ነው፡፡

የምርጫ ቦርድ እጩ ተወዳዳሪዎች የስራ ቋንቋ ያልሆነው የሌሎች ብሄረሰቦችን ቋንቋ ለመመረጥ ማወቅ አለባችሁ ብሎ መወሰኑ በቋንቋ ምክንያት በብሔረሰቦች መካከል ልዩነት መፍጠርና የመምረጥና መመረጥ መብታቸውን የሚሸራርፍና የሚገድብ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ዜጎች በሚመለከታቸው አስተዳደራዊ ጉዳይ ሁሉ አቀፍ ነፃ ፍትሀዊ በሆነ ሂደት ውስጥ እንዳይሳተፉ ማድረጉ

የዜጎች መሰረታዊ የዲሞክራሲን መብት የሚሸራርፍና የሚገድብ ከመሆኑም በላይ ለረጅም ጊዜ አብረው የኖሩትን ሕዝቦች መከፋፈሉ በክልልም ሆነ በአገር ደረጃ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የብሔር ብሔረሰቦችና የግለሰቦች መብትና እኩልነት የተረጋገጠበት በመተሳሰብና በወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚደረገውን ሂደት የሚያደናቅፍና አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ስለዚህ የምርጫ ቦርድ ውሳኔ ከሕገመንግስቱ አላማዎችና ግቦች በተለይ ደግሞ ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 38 ጋር የሚቃረን ስለሆነ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9 መሰረት ተፈፃሚነት የለውም፡፡

## የውሳኔ ሀሳብ

1. በቤንሻንጉልጉሙዝ ክልል በመምረጥና መመረጥ ዙሪያ ለቀረበው ህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የምርጫ አዋጁ አንቀጽ 38 ሕገመንግስቱን የማይጻረር ከመሆኑም በላይ ማንኛውም ለመመረጥ የሚፈልግ ዜጋ ማሟላት ያለበትን መስፈርት በማስቀመጥ እና ሁሉንም ዜጎች በእኩል አይን የሚያይ ሕግ መሆኑን በማረጋገጥ፣
2. የቤንሻንጉል ጉሙዝ የክልሉ ብሔራዊ ቋንቋ አማርኛ መሆኑን የክልሉ ሕገመንግስት የደነገገ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት፣
3. የሕገመንግስቱ ፖለቲካዊ ትርጉም ቋንቋን በዘረኝነት መንገድ መጠቀም እንደማይቻል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአካባቢው የስራ ቋንቋ (ም/ቤቱ የሚሰራበት የስራ ቋንቋ) ወይም የክልሉ

ብሔራዊ ቋንቋን ማወቅ ለምርጫ እንደመመዘኛ መጠቀም ተገቢ መሆኑን በመረዳት፣

4. በዚህም መሰረት በአንድ አካባቢ በሚደረግ ምርጫ ምክር ቤቱ የሚሰራበትን ቋንቋ ወይም ከሚሰራባቸው ቋንቋዎች አንዱን ማወቅ እንደመመዘኛ መውሰድ ተገቢ በመሆኑ፣ (ለምሳሌ በሐረሪ ክልል ሐረሪኛና ኦሮሚኛ)፣
5. በተለያየ ደረጃ በሚገኙ ምክር ቤቶች በእጩነት ለመመረጥ የምክር ቤቶቹን የስራ ቋንቋ ማወቅ እንደ አንድ መስፈርት መቀመጡና በሕግ መደንገጉ ሕገመንግስቱን እንደማይቃረን በማረጋገጥ፣
6. ሆኖም ግን በፌዴራል ፓርላማ ለመመረጥ የሚቀርብ ዕጩ ተመራጭ የክልሉን የአካባቢውን ቋንቋ ማወቅን እንደ መመዘኛ ወይም እንደ መስፈርት ማስቀመጥ ከሕገመንግስቱ ፖለቲካዊ ትርጉም ጋር ስለማይጣጣም ለፌዴራሉ ፓርላማ እጩ ተመራጭ ሆኖ ለሚቀርብ የክልሉን ብሔራዊ ቋንቋ ማወቅ እንደመስፈርት መቀመጥ እንደሌለበት በመገንዘብ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## <u>የተሰጠ ውሳኔ</u>

1ኛ. የምርጫ ቦርድ ውሳኔ የካቲት 10 ቀን 1992 ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ በአሶሳ ዞን በሚገኙ በባምበሲና በአሶሳ የምርጫ ክልሎች የተመዘገቡትን እጩ ተወዳዳሪዎች የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች ቋንቋ ከሆነው አንዱን ማለትም

የበርታን ቋንቋን አትችሉም በማለት ከምርጫ እንዲታገዱ የሰጠው ውሳኔ የኢፌዲሪ ሕገመንግስቱን የሚቃረን መሆኑን በማረጋገጥ በዛሬው እለት ማለትም መጋቢት 5 ቀን 1995 ዓ.ም በኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ3ኛ አመት የስራ ዘመኑ በሁለተኛ መደበኛ ስብሰባው ባካሄደው ውይይትና በደረሰበት መደምደሚያ መሰረት ከላይ የተጠቀሰው የምርጫ ቦርድ ውሳኔ ሕገመንግስቱን የሚቃረን ስለሆነ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ወደፊት በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2ኛ. ማንኛውም የፌዴራሉም ሆነ የክልል መንግስት አካል ይህን የፌዴሬሽን ም/ቤት ውሳኔ እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡

ስብሰባው 12፡40 ላይ ተጠናቋል፡፡

# ክፍል 2

## በአመልካች ወ/ሮ ከድጃ በሽር የሕገ መንግስታዊ መብት መከበር አቤቱታ ላይበፌዴሬሽን ም/ቤት የተሰጠ ውሣኔ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ 2ኛው የፌዴሬሽን ምክር ቤት 4ኛ አመት የስራ ዘመን ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ግንቦት 7 ቀን 1996 ዓ.ም ቀጥሎ የዋለ ሲሆን ክቡር አፈ ጉባኤው ቀጣዩ አጀንዳ ከህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የህገ መንግስት ትርጉም ጉዳይ ላይ ቤቱ ተመልክቶ ውሳኔ መስጠት ስለሚሆን የውሳኔ ሀሳቡ አስቀድሞ የተሰራጨና የተነበበ መሆኑ ታስቦ የሕገ መንግስትና ክልል ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም ክቡር አቶ ዳንኤል ደምሴ የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ የህገ መንግስትና ክልል ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የተመለከታቸውን ፍሬ ሃሳቦች የወ/ሮ ከድጃ በሽር ጉዳይን በሚመለከት ከሶስት ተከሳሾች ጋር ለኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ውክልና በሰጡት መሰረት የባለ ጉዳይዋን ክስ ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርበው መከራከራቸውን ጠቁመው የምክር ቤቱዋና ፍሬ ሀሣብ የሚሆነው በህገ መንግስት ትርጉም ጉዳይ እንጂ በአቤቱታ አቅራቢና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ባለመሆኑ ሕገመንግስቱን መሰረት በማድረግ ጉዳያቸው በሸርያ ፍርድ ቤት

በሚታይበት ሁኔታ ላይ ተከሳሾች አዋጅ ቁጥር 250/93/ አንቀጽ 17፣20፣23 እና 22 በአዋጅ ቁጥር 251/93 አንቀጽ 4/1/ የሕገመንግስቱን አንቀጽ 34/5 በመጥቀስ በሸርያ ህግና ፍርድ ቤት መዳኘት እንደማይፈልጉ ጠቁመው የሕገመንግስቱን አንቀጽ 34/5 ‹‹ ... በተከራካሪዎች ፈቃድ በኃይማኖት ወይም በባህሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡..›› የሚል ስለያዘ ይህንኑ መሰረት በማድረግ አግባብ አለመሆኑን ያቀረቡት መንግስት በበኩሉ የሸርያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው በእስልምናው ሃይማኖት ለመዳኘት በግልፅ በፍቃዳቸው መርጠው የቀረቡ እንደሆነ ነው በሚል ስለተቀመጠ ጉዳዩ የቀረበለት የሸርያ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቶበት የጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤትም ይግባኝ ቀርቦለት ውሳኔውን ያፀደቀው መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

አክለውም ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲለወጥ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ አቤቱታው ተቀባይነት ማጣቱንና በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9/1/ ድንጋጌ መሰረት ከሕገመንግስቱ ጋር የሚቃረን ውሳኔ የተሰጠበት ሆኖ በመገኘቱ የሕገመንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤ የሰጠውን የውሳኔ ሀሳብ የሕገመንግስትና የክልል ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የተመለከተውና ክርክሩ በቀረበበት ጊዜ የተጠቀሰው አዋጅ በስራ ላይ ስለነበር ውሳኔ ሊሰጡ መቻላቸውን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 34/5/ መሰረት ተከሳሾቹ የጠቀሱትን አንቀፅና መመሪያ በመቀበል መዳኘት ሲገባቸው የሕገመንግስቱ አንቀፅ 34/5/ ተፈፃሚነት ዝርዝር ህግ ከወጣ በኋላ እንደሆነ ወደፊትም የሚወጣው ህግ በስራ ላይ ካልዋለ ተከሳሽ

ተጠርቶ በሚቀርብበት ጊዜ በስራ ላይ የዋለ ቢሆንም ለክርክሩ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው አድርገው ለሕገመንግስቱ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠታቸው ከዳኝነት ስልጣናቸው የዘለለ በመሆኑ የሕገ መንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤ ከስር ፍርድ ቤቶች ጀምሮ እስከ ላይኛው ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ የሄደበትና በጥልቀት የመረመረበት ሁኔታ ስለታየ በአዋጅ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በተሰጠው ስልጣን መሰረት ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ህገመንግስቱን የሚቃረን በተለይ አንቀፅ 13 እና አመልካቾች ያቀረቡትን የመቃወሚያ አንቀፅ 34/5/ የሚጥስ ሆኖ መገኘቱን የሚዘረዝሩበትን የውሳኔ ሀሳብ ስላቀረቡ የሕገመንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ ምክር ቤቱ ሊያፀድቀው ወይም ሊሽረው ስለሚችል ጉዳዩ መቅረቡን ገልፀዋል፡፡

ክቡር አቶ ፀጋዬ ማሞ በበኩላቸው የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ አሳማኝና ብዙ የማያከራክር ስለሆነ የሕገመንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው እውነትነት ያለው በልዩነት ያልቀረበ በጋራ የተወሰነና ከሴቶች መብት አንፃር ሲታይ ትርጉም ያለው ስራ በመሆኑ በቀረበው መንገድ ቤቱ እንዲቀበለው ጠይቀዋል፡፡

በማስከተል ክቡር ዶ/ር ሰለሞን እንቋይ የሸሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ህገ መንግስቱን የጣሰ ለመሆኑ በማያሻማ ሁኔታ በመቅረቡ የሕገመንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤን የውሳኔ ሀሣብ ተቀብለን ብናሣልፈው የተሸለ ነው ብለዋል፡፡

ክቡር አቶ ደሣለኝ ደመቀ በበኩላቸው ለናኢባ 3ኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ የተመሠረተው ህዳር 14 ቀን 1992 ዓ.ም ቢሆንም ተከሣሾቹ በሸሪያ ሕግና ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የገለጹት ታህሳስ 14 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑን ግንዛቤ ስላለ ተከሳሾቹ መጀመሪያ ወደ ክርክር ገብተው ወይም ክርክሩ ሳይጀመር ቆይቶ አንሰማማም ብለው ጉዳዩን ያነሱ ከሆነ በአንድ ወር ጊዜ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጠይቀዋል፡፡

ከዚያም ክቡር አቶ ዳንኤል ደምሴ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ በክርክር ደረጃ በፍርድ ቤቶች ጉዳዩ የተጀመረው ህዳር 14 ቀን 1992 ዓ.ም ሆኖ መቃወሚያና ክሱ በተመሳሳይ ጊዜ በሸሪያ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆናቸውንና በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀደም ብሎ ፋይል በመክፈቱ የተከራከሩበት በታህሣስ 14 ቀን 1992 ዓ.ም መቃወምያ መፃፋቸውን ገልፀው ህዳር 14 ቀን 1992 ዓ.ም ደግሞ የሸሪያ ፍርድ ቤትን ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ቀድሞ ስራ ላይ የዋለና የተደነገገ ስለሆነ በሁለቱ ፍቃድ ካልተቀመጠ በስተቀር ፍቃዳቸውን ካልገለጹ ለመዳኘት አይገደዱም ብሎ ደንብ ወጠቶ የነበረውን አዋጅ ወደፊት አሳልፊው ወደ ኋላ ተመልሶ አይሠራም በሚል ስህተት መፈፀሙን ገልፀዋል፡፡

በመቀጠል ክቡር አቶ አታክልቲ ግደይ ከቀረበው ሀሣብና ጥያቄ እውነታ አንፃር ልዩነት ያላቸው ሆኖ ክሱ እንደመጣ መነሻ የሆነው ከናኢባ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ድረስ እንዲታይ አቤቱታ ቀርቦበት የመጀመሪያው ውሳኔ እንዲፀድቅ የተገደዱበት ሁኔታን አውስተው ከሣሽ ሆነው የቀረቡት ሰዎች ኅዳር 14 ቀን 1992 ዓ.ም ማመልከቻቸውን ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሕገመንግ ስታዊ መብቴ ተጥሷል ብለው አቤቱታ ያቀረቡት ወ/ሮ ከድጃ በሽር በፍርድ ቤት ተከሰው መጥሪያ ተሰጥቷቸው መልስ እንዲሰጡ የቀረቡት ታስሣስ 14 ቀን 1992 ዓ.ም ሲሆን የሸሪያ ፍርድ ቤት አዋጅ ደግሞ ኅዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም ወደ ተግባር ተለውጧል፡፡ የናኢባ ፍርድ ቤት ለቀረበው አቤቱታ ውሳኔ የሰጠበት ምክንያት የፌደራል ሸሪያ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4 ንዕስ ቁጥር 2 ላይ ‹‹…ተከራካሪ ወገኖች በእስልምናው ሃይማኖት ስርአት ለመዳኘት ግልፅ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ከሆነ ብቻ ይሆናል›› ስለሚል የሕገመንግስቱን ድንብ ያካተተ ነው፡፡ የሸሪያ ፍርድ ቤት ማጠናከሪያ አዋጅ ከሕገመንግስቱ ጋር የሚሄድ አንቀፅ ቢኖረውም ባይኖረውም በሕግ ተዋረድ ሕገመንግስቱ የበላይ ሆኖ በሕገመንግስቱ መገዛት ሲገባው ሕገመንግቱን ማጣቀስ ተስኖት ከሕገመንግስቱ በመነጨ ሕግ የሚውለውን ብቻ ይዞ መሄድ ግጭት ያመጣል ብለዋል፡፡

አያይዘውም የሕገመንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤም ተከሳሾች በሃይማኖታቸው ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆናቸውን መግለፅ የሚችሉበት በተጠሩበት ታህሳስ 14 ቀን 1992 ዓ.ም ሆኖ በቀረቡበት ጊዜ ደግሞ በሀይማኖቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ አለመሆናቸውን ገልፀው እያለ ይህን ችላ ብሎ በሸሪያ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛነታቸውን ገልፀው ሳይሆን መጨረሻ ላይ የሚያመቻቸው ሆኖ ሲያገኙት ከመጀመሪያው ሕገመንግ ስቱ ሁለት ዕድል ሰጥቶ ስፈልግ በመደበኛው ፍርድ ቤት ካልሆነ በሃይማኖት በልማዳዊ አሠራር መሄድ እችላለሁ ብለው እያለ ማለትም ሕገመንግስቱ በአንቀጽ 34 ንዑስ ቁጥር 5 መሠረት ማንኛውም ሰው ሕገመንግስቱን በማይፃረር መልኩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሀይማኖታዊ ልማድ ፈቃዱን ገልፆ እዳኛለሁ ብሎ ከገባ አይከለከልም የሚለውን ፍቃዳቸውን በገለጹበት ጊዜ ለማስኬድና ችሎቱን ለማስቻል የተሞከረ ስለሆነ የሕገመንግስት አጣሪ ጉባኤን መሰረት በማድረግ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 13/1/ የፍትህ አካላት የሕገ መንግስቱን መሠረታዊ መርሆዎ የማስፈፀም ገዴታ ያለባቸውና ሕገመንግስቱን የሚፃረር ልማዳዊ አሠራር በሚኖርበት ጊዜ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ ‹‹…ማንኛውም ህግ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሣኔ ከዚህ ሕገመንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡›› በሚል መንገድ ተከትሎ ሕገመንግስቱ ያስቀመጠላቸውን ፈቃዳቸውን ገልፀው ለመዳኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሲገባው አስገድዶ ውሳኔውን እንዲቀበሉ

ማድረግ ሕገመንግስቱን የሚፃረር ስለሆነ የሕገመንግስት ጉዳዬች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ የሕገመንግስትና ክልል ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴም አሳማኝ ሆኖ ስላገኘው የውሳኔ ሀሳቡ በምክር ቤቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጠይቀዋል፡፡

በመቀጠል ክቡር ዶ/ር ሙላቱ ተሸመ ሕገ መንግስቱ ለዜጎች የሰጠውን መብት መሠረት ተደርጎ የተሰጠው የውሳኔ ሀሣብና በሕግ አተናተኑ ብስለት ያለው ትንተና የቀረበበት በመሆኑ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ቤቱ እንዲቀበለው ለድምፅ አቅርበዋል፡፡ በዚህም የውሳኔ ሀሳቡ ከአንድ ድምፀ ተአቅቦ በስተቀር ቤቱ በሙሉ ድምፅ ተቀብሎ አፅድቆታል፡፡

## ክፍል 3

## በስልጤ ህዝብ የማንነት ጥያቄ ላይ የፌዴሬሽን ም/ቤት የሰጠው ውሳኔ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ለህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቁጥር ሕ/ተ/ም-ፌ15/40/3/1 ጥር 17 ቀን 1992 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ፡-

የአንድን ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ መወሰን ያለበት ማን ነው? የሚወሰንበት ስነስርዓት ምን መሆን አለበት? በማለት አቅርቦ በዚህ ላይ የውሣኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ጠይቋል፡፡

በዚህ መሰረት አጣሪ ጉባኤው የስልጤ የማንነት ጥያቄዎች ላይ የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ጥያዌዎቹ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማመን እንደሚከተለው ተመል ክቷል፡፡ ከዚህም በመነሳት የውሳኔ አስተያየት ለመስጠት ያመች ዘንድ የሚከተሉትን ጭብጦች በማውጣት ውይይት ካካሄደ በኋላ በጭብጦቹ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ሰጥቷል፡፡

**ጭብጦች**

የአንድን ማሕበረሰብ የማንነነት ጥያቄ መወሰን በኢፌዴሪ ሕገመንግስት መሠረት የማን ሥልጣን ነው? የሚወሰነውስ ምን ዓይነት ስርዓት በመከተል ነው? የሚሉ ሲሆኑ በመቀጠል ጉባዔው በእነዚህ ጭብጦች ላይ በስፋት ተወያይቷል፡፡ በዚህም መሠረት ቀጥሎ የተገለጸውን አስተያየት አቅርቧል፡፡

## የውሳኔ ሐሳብ

ጉባዔው በኢፌዴሪ ሕገመንግስት ውስጥ ያሉትን የብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት አስመልክቶ የተደነገጉትን የህገመንግስቱ አንቀጾች አንድ በአንድ በማንሳት በሰፊው ተወያይቶበታል፡፡ በዚህም መሠረት በሕገ መንግስቱ አንቀድ 39/5/ መሠረት ብሔር ብሔረሰብ ተብሎ ለመፈረጅ መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ከተመለከተ በኃላ አንድ ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ በማንሳት ብሔር ለመባል የሚፈለጉትን መስፈርቶች ያሟላሁ ስለሆነ እውቅና ይሰጠኝ እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዙ መብቶች ይከበሩልኝ የሚል ጥያቄ

ሲያነሳ ይህን ጥያቄ ተመልክቶ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የማነው? የሚለውን ለመመለስ ተሞክሯል በዚህም መሰረት ይህንን ጥያቄ በቀጥታና በግልፅ የሚመልስ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ የሌለ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ላይ አግባብነት ያላቸውን የህገመንግስቱን ድንጋጌዎች አንቀፅ 39/4/፣ 47/3/፣ 52/2/ /ሀ/ ፣62/3/ አንድ በአንድ ከጉዳዩ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በመነሳት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ጥያቄ መወሰን አስመልክቶ በሚነሳው ጥያቄ ረገድ በመጀመሪያ አንቀፅ 39/4 መርምረናል፡፡ ይህ የህገመንግስቱ አንቀፅ ብሄር ብሄረሰቦች የሚያነሱትን የመገንጠል ጥያቄና የአፈፃጸም ስርዓቱን ይደነግጋል፡፡ በአፈፃፀሙም የክልሉና የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጋራ ሚና ኖሯቸው በየድርሻቸው እንደሚሳተፉ ደንግጓል ስለሆነም ይህ ድንጋጌ ብሄር ብሄረሰቦች የሚያነሱትን የመገንጠል ጥያቄ የሚመለከት እንጂ አንድ ማህበረሰብ የሚያነሳውን የማንነት ጥያቄ የሚመልስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመቀጠልም የህገመንግስቱን አንቀፅ 47 ስንመለከት ደግሞ እንዲሁ በብሄር ብሔረሰብነት ማንነታቸው ታውቆ በክልሉ ውስጥ የቆዩ ሆነው ነገር ግን የራሳችንን ክልል እናቋቁማለን የሚል ጥያቄ ለክልል ምክር ቤት ቀርቦ በዚያው የሚፈፀም መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይህ ድንጋጌ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡

በመቀጠል ደግሞ የሕገመንግስቱ አንቀድ 52/2 /ሀ/ እና 62/3/ ድንጋጌዎች ተመልክተናል፡፡ በዚሁም መሰረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 52/2//ሀ/ የማንነትን ጉዳይ የመወሰን ስልጣን የማን እነደሆነ በግልፅ የማያስቀምጥ ይሁን እንጅ የክልሎች ስልጣን ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ ተገልጿል፡፡ ይህንን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ክልሉ የቋንቋን አሰፋፈርን እና የማንነትን መሰረት የተከተለው የፌደራል መንግስት አወቃቀር መልክ አምድርን ብቻ መሠረት ያደረገ ሳይሆን ቋንቋንም የሚጨምር በመሆኑ ነው፡፡

ስለዚህም ክልሎች ራስን በራስ ማስተዳደር አላማው ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር በሚያዋቅሩበት ጊዜ በቅድሚያ የማንነትን ጥያቄ መወሰን የሚጠበቅባቸው ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህገ መንግስቱ የተከተለው ፌደራላዊ የአወቃቀር ስርዓት ለክልሎች በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጥ በመሆኑ የማንነት ጥያቄ በክልሉ ውስጥ የሚነሳ ጉዳይ እንደመሆኑ የክልሉን ውሳኔ ማግኘት የግድ ይሆናል፡፡ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በመነሳት ጉዳዩን ስንመለከተው ማንነቴ ይታወቅልኝ በማለት በአንድ ማህበረሰብ የሚቀርብ ጥያቄ በቅድሚያ ቀርቦ መስተናገድ የሚገባው ጥያቄው በተነሳበት ክልል ምክር ቤት መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፤ በሌላ በኩል ደግሞ የህገመንግስቱን አንቀድ 62/3/ ስንመለከት የፌደሬሽን ምክር ቤት የእራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በህገመንግስቱ መሰረት

ይወሰናል ይላል፡፡ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የፌደሬሽን ምክር ቤት እስከ መገንጠል ድረስ ባሉ የማንነትን ጥያቄ ጨምሮ የብሄር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መብት ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እንዳለው ይደነግጋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከአንቀጾቹ ድንጋጌ የምንገነዘበው አጠቃላይ ሃሳብ ማንነትን አስመልክቶ አንድ ማህበረሰብ በሚገኝበት ክልል ምክር ቤት ሆኖ በክልሉ የነበረውን የአፈፃፃም ሂደት ጉድለት አለበት ወይም ህገመንግስቱን መሰረት አድርጎ አልተፈፀመም የሚል ቅሬታ ሲነሳና በዚህ እና ተመሳሳይ ምክንያቶች ጥያቄውን በአቀረበው ማህበረሰብ እና በክልሉ ምክር ቤት መካከል ልዩነት ሲኖር ጉዳዩ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደሚቀርብ እና ምክር ቤቱ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሰጥበት ነው፡፡ በአፈፃፀም ሂደት ላይ የህገመንግስቱ መንፈስ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሲሆን እዚህ ላይ መታየት ያለበት ቁም ነገር ማንነቴ ይታወቅልኝ በማለት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሰጪው ጥያቄ አቅራቢው ማህብረሰብ እንደሆነም የክልሉ እና ፌዴሬሽኑ ምክር ቤቶች በዚሁ ጉዳይ አወሳሰን የሚኖራቸው ሚና ይህንን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የእነዚህ ምክር ቤቶች ሚና ጥያቄው ቀርቦ ፍፃሜ እስኪያገኝ ድረስ ያለው ሂደት ህገ መንግስቱን ተከትሎ እንዲፈፀም ማድረግ ይሆናል፡፡ በአጠቃለይ ማንነቴ ይታወቅልኝ በማለት የሚቀርብ ጥያቄ ጉዳዩ ከተነሳበት ክልል ጀምሮ

እንደአስፈላጊነቱ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ድረስ በመቅረብ ውሳኔ ሊያገኝ የሚችል መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም የማንነትን ጥያቄ አስመልክቶ በሚነሳ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው ህገ መንግስቱ የተቀረፀበትን መንፈስ እና ህገመንግስታዊ መርሆዎቹን በመከተል ይፈጸም ዘንድ የሚቀርበው ጥያቄ የማህበረሰቡ ትክክለኛ ጥያቄ መሆኑን ማሳየት እንዲችል በአንቀፅ 39/5/ የተመለከቱት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን ማሳየት ጥያቄው በፅሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ አንቀጽ 39/5/መስፈርቶችን ያገናዘበ ጥናትን መሰረት በማድረግ ለህዝብ ውሳኔ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል ፡፡ ህዝበ ውሳኔው ዲሞክራሲያዊ እና ፍትሃዊ እንዲሆን ጥያቄውን ያቀረበው ማህበረሰብ አባላት በቀጥታ የሚሳተፉበት፣ ነፃ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርዓት እንዲሁም ገለልተኛ ታዛቢዎች በተገኙበት አግባብ ሊከናወን ይገባል፡፡

የማንነቱ ይታወቅ ጥያቄ ጥያቄውን ያቀርበው ማህበረሰብ አባላት በሚያደርጉት ቀጥተኛ ተሳትፎ በሕዝበ ውሳኔ መወሰን ይገባዋል የተባለበት ዋነኛ ምክንያቶች፡-

የማንነት ጥያቄ የብሔር ብሔረሰቦች ወይም ሕዝቦች መብቶች መሰረትና ምንጭ በመሆኑ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጥያቄ ስለሆነ፣ መሰል ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የመገንጠልና ክልልን የመመስረት ጥያቄዎች የሚወሰኑት ህዝቡ በሚያደርገው ቀጥተኛ

ተሳትፎ በሕዝበ ውሳኔ እንደሆነ የህገ መንግስቱ አንቀድ 39/4/ እና 47/3/ ስለሚደነግግ ነው፡፡

የማንነት ጥያቄ የእያንዳንዱን የማህበረሰብ አባል ማንነት የሚነካና የሚመለከት በመሆኑ የአብዛኛውን የማህበረሰቡን ፍላጎት በትክክልና በአስተማማኝ መልኩ ለማወቅ የሚያስችለን ስርዓት ነው፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ማንነት አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ በማንና እንዴት መወሰን አለበት? በሚለው ህገመንግስታዊ ጉዳይ የተሰጠው የህገመንግስቱ ትርጉም ከፍ ሲል የተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረት የስልጤ ማህበረሰብን ማንነት ለማስወሰን የቀረበው ጥያቄ በትርጉሙ ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች እና አፈፃፀም መከተል በሚገባው ሂደት ላይ በመመስረት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## የሃሳብ ልዩነት

እኛ በሃሳብ የተለየነው የጉባኤ አባላት፣ የማንነት ጥያቄ ሲነሳ የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች የሚኖራቸውን ሚና አስመልክቶ አብዛኛው በሰጠው አስተያየት እንስማማለን፡፡ የአፈጻጸሙን ስርዓት በሕዝበ ውሳኔ መሆን አለበት በሚለው ግን ቀጥሎ በሰጠነው ምክንያት ተለይተናል፡፡

የሕዝብ የብሔር ወይም የብሔረሰብ ማንነት አከራካሪ ሲሆን የመጨረሻው ውሣኔ ሰጪ ሃይል ሕዝቡ ራሱ መሆን እንዳለበት

እናምናለን፡፡ ይህ የሚሆንበት ግን የመጨረሻው የስልጣን ባለቤት ሕዝቡ ራሱ ከመሆኑ በሚመነጭ ምክንያት እንጂ ሕገመንግስቱ እንዲዚህ አይነት ጥያቄዎች በህዝበ ውሳኔ ማለቅ አለባቸው ስለሚል አይደለም፡፡ ሕገመንግስቱ ሕዝበ ውሳኔን የግድ የሚለው በተወሰኑ ተለይተው በተቀመጡ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡ /አንቀድ 47 እና 39ን ይመለከታል/፡፡ ከዚህ ውጪ የሚነሱ ጥያቄዎች መፈታት የሚኖርባቸው በሕገመንግስቱ ነው፡፡ ሕገመንግሥቱ ደግሞ ሕዝብ መብቱን በቀጥታ ወይም በተወካዮቹ በኩል ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው የማንነት ጥያቄ ቀጥተኛ በሆነ /ሕዝበ ውሳኔ/ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ምላሽ እንዲያገኝ ማድረጉ የሕገመንግስቱን መርህ የተከተለ መሆኑን ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገር የሕዝብን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ፍትሃዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ሕጋዊ የአፈጻጸም ሥርዓት ተግባራዊ መሆኑን መከተል ይመስለናል፡፡ በዚህ ምክንያት ከሕዝበ-ውሣኔ በመለስ ያለው አፈጻጸም ህገመንግስቱን የሚጥስ ነው ማለት የሚቻል አይመስለንም፡፡ ስለዚህ የማንነት ጥያቄ በሕዝበ-ውሣኔ እልባት ሊያገኝ ይገባል የሚለው የአብዛኛው ድምጽ አስተያየት ሌሎች ዴሞክራሲያዊ አካሄዶችን ግምት ውስጥ ያስገባ ስላልመሰለን በድምጽ ተለይተናል፡፡

ከዚያም ክብርት አፈጉባዔዋ ቤቱ የሕገመንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባዔ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብና የክልሎችና የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚያቀርበው አስተያየት ላይ ውይይት

ቢደረግ የተሻለ እንደሆነ በመጠቆም ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት ለቤቱ እንዲያቀርብ ጋብዘዋል፡፡

ክቡር አቶ ሐሰን ሽፋ በበኩላቸው የክልሎችና የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚያቀርበው አስተያየት በአጣሪ ጉባዔው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተመረኩዞ በመሆኑ በቅድሚያ አጣሪ ጉባዔው ግልጽ ባልሆኑ ነጥቦች ዙሪያ ማብራሪያ ቢሰጥ የተሻለ እንደሆነ ጠቁመዋል ፡፡

በመቀጠልም ክብርት አፈጉባኤዋ የቤቱን ውይይት አቅጣጫ ለማስያዝና የክልሎችና የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከአጣሪ ጉባኤው በተሻለ አንድ ተጨማሪ ጊዜ ወስዶ በጉዳዩ ላይ ስለተወያየበት እንዲሁም ቤቱንም በተደራጀ ሀሳብ ላይ ውይይት ቢያደርግ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስፈልገውን ጊዜ ስለሚያሳጥር የኮሚቴው አስተያየት ለቤቱ ቢቀርብና ውይይቱ ቢካሄድ የተሻለ እንደሆነ፣ ይህም ሆኖ ግን ቤቱ ከአጣሪ ጉባኤው ሊያገኝ የሚፈልገውን ማብራሪያ እንደማያሳጣው ጠቁመው በአካሄድ ላይ አስተያየት ካለ እንዲቀርብ ቢጠይቁም ባለመቅረቡ የኮሚቴው ሊቀመንበር ክቡር አቶ አህመድ ሰይድ ኮሚቴው የማንነት ጥያቄ በማንና እንዴት እንደሚወሰን ያለውን አስተያየት እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

# በህገ መንግሥትና ክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ

## የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ

በልዩ ልዩ ክልሎች በሚገኙ አንዳንድ ማህበረሰቦች ሊነሱ ስለሚችሉ የማንነት ጥያቄዎች በሕገመንግሰቱ መሠረት እንዴት መወሰን እንዳለበት የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማመን የውሳኔ ሀሣብ ባቀረበባቸው ሁለት ጭብጦች ማለትም፡-

ሀ. የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ጥያቄ መወሰን በኢፌዴሪ ህገመንግሥት የማን ስልጣን ነው?

ለ. የሚወሰነው ምን ስነሥርዓት በመከተል ነው?

በሚሉት ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የህገ መንግሥትና ክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ተወያይተንባቸው የራሳችንን የውሳኔ ሐሳብ እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

በአጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሐሳብ ውስጥ የተካተቱትን የኢፌዴሪ ህገመንግሥት አንቀጾች ማለትም 39/5/፣ 39/4/፣ 47/3/፣ 52/2/ሀ/፣ 62/3/ ከላይ ከተጠቀሱት ጭብጦች በምን አግባብ ሊገናኙ እንደቻሉ መገንዘብ ያስችለን ዘንድ በዝርዝር ከጉዳዩቹ ጋር እያገናዘብን አንድ በአንድ ያየን ሲሆን፣ በጭብጦቹ ላይ የአጣሪ ጉባኤውን የብዙሃንና የአናሳ ሀሳብ ካየን በኃላ የብዙሀኑን ሃሳብ በስብሰባው የተገኘነው የክልሎችና የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ያለ ልዩነት ተቀብለዋል፡፡

ማንነትን አስመልክቶ በማንና እንዴት መወሰን እንዳለበት ከዚህ ባላይ በተራ ቁጥር 1 ባቀረብነው ሃሳብ ውስጥ ምላሽ የሚያገኝ ቢሆንም፣ የማንነት ጥያቄ ጥያቄው በቀረበ በምን ያህል ጊዜ ይወሰን የሚል ጭብጥ በዚህ ያልተካተተ በመሆኑ ኮሚቴው ሃሳብ ሊያቀርብበት እንደሚገባ አምኖበታል፡፡

ስለሆነም ለማነፃፀር ይቻል ዘንድ አግባብነት ያላቸውን የህገመንግሥቱን አንቀጾች ማለትም አንቀድ 39/4 /ለ/ እና 47/3/ለ/ን ተመልክተናል፡፡

በአንቀጽ 39/4 /ለ/ መሠረት የመገንጠል ጥያቄ የብሔር ብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሦስት አመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ሕዝበ ውሣኔ የሚያደራጅ ሲሆን፣ በአንቀጽ 47/3/ /ለ/ መሰረት ደግሞ ‹‹የማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ ወይም ህዝብ የራሱን ክልል የመመሥረት መብት ሥራ ላይ የሚውለው ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፤ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ህዝበ - ውሣኔ ሲያደራጅ ነው›› ይላል፡፡

ስለዚህ በህገ መንግስቱ የመገንጠል ጥያቄ በቀረበ በሦስት ዓመት፣ ክልል የመመሥረት ጥያቄ ደግሞ ጥያቄው በቀረበ በአንድ አመት ጊዜ ህዝበ ውሳኔ የሚያደራጅ ከሆነ፣ የማንነት ጥያቄ ዕውቅና የማግኘት ጥያቄ ብቻ በመሆኑ ከመገንጠል ጥያቄና ክልል

ከመመስረት ጥያቄ አንጻር ሲታይ ያነሰ ጊዜ የሚበቃው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የማንነት ጥያቄን  የመወሰኛ ጊዜን በተመለከተ ጥያቄው የቀረበለት ምክር ቤት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ህዝበ ውሳኔ ሊያደራጅ ይገባል የሚል የውሳኔ ሐሳብ በስብሰባው የተገኘነው የኮሚቴው  አባላት አቅርበናል፡፡

በአጠቃላይ በልዩ ልዩ ክልሎች የሚገኙ አንዳንድ ማህበረሰቦች ማንነትን አስመልክቶ ሊያነሱት የሚችሉት ጥያቄ በማን፤ እንዴትና በምን ያህል ጊዜ መወሰን እንዳለበት ከዚህ በላይ ባቀረብነው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት መወሰን የሚችል መሆኑን እየገለጽን፣ በአሁኑ ጊዜ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ ያለው የስልጤ ማንነት ጥያቄ ከዚህ በላይ ባለው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት የክልሉ ምክር ቤት ገምግሞ ምላሽ ይሰጠው ዘንድ በቅድሚያ ለክልሉ ዕድል እንዲሰጥ ሀሳብ  እናቀርባለን፡፡

ከዚያም ክብርት አፈ-ጉባኤዋ ወ/ሮ አልማዝ መኮ የማንነት ጥያቄ እንዴት እና በማን ይወሰናል የሚለውን በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያ እንደተሰጠ ይኸውም የማንነት ጥያቄን ምላሽ ለመስጠት በቅድሚያ የክልል ምክር ቤቶች ትልቅ ሚና እንዳላቸውና  በዚህ ደረጃ በተወሰነው ውሣኔ ቅሬታ ወይም የሀሳብ ልዩነት   ሲፈጠር ደግሞ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሊታይ እንደሚችል በዚሁ መሠረት የስልጤ የማንነነት ጥያቄ ክልል የመመስረት ወይም የመገንጠል ባለመሆኑ በ6ወር ጊዜ ውስጥ በክልሉ እንደገና ታይቶና መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

ተሟልተው የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኝ የሚያመለክት ሃሳብ መቅረቡን አመልክተዋል፡፡

የፌዴሬሽን ም/ቤትም በሕገመንግስቱ የተቀመጠው ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ያላቸውን አቅም ማጎልበት የሚለውን መርህ ከማሳካት አንፃር ለክልሎች የተሰጠውን ራስን በራስ የማስተዳደርን ዓላማ መሰረት ያደረገ መስተዳድር የመመስረት ሀላፊነት እንዲጠናከር፣ ስለሆነም ክልሎችን ማዋቀር ብቻ ሳይሆን ራሣቸውን በራሳቸው በሚያስተዳደሩበት ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን እየፈቱ እንዲሄዱ እገዛ ከማድረግ አኳያ ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቅሰው የስልጤ የማንነት ጥያቄ ከሕገመንግስታዊ መርሆዎች አንፃር በክልሉ እንዲታይ በሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በቀረበው የውሳኔ ሃሣብና የክልሎችና የህገ መንሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በቀረበው አስተያየት ላይ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካለ እንዲቀርብ መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

በመቀጠልም ክቡር አቶ ማቴዎስ ሐንቀሎ የስልጤን ማንነት አስመልክቶ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ያስተላለፈው ውሣኔ በፌዴሬሽን ምክር ቤት በኩል እንደገና እንዲታይ የተደረገው ምን ጉድለት ቢኖርበት ነው? በተጨማሪም የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም የስልጤን ማንነት አስመልክቶ በቅርቡ የሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እርስ

በራሳቸው የሚጋጩ ሃሳቦች መያዙን በአጠቃላይ የአጣሪ ጉባኤው የስራ ቅንጅት ምን እንደሚመስል እንዲብራራ ጠይቀዋል፡፡

በማስከትልም ክቡር አቶ ዓለማየሁ አለሙ በሀገራችን የክልሎችን የራስ በራስ የማስተዳደር ስልጣንን አስመልክቶ በማንነታቸው፤ በባህላቸው፤ በስነ ልቦናና በቋንቋቸው አንድ ነን ብለው የሚያምኑ ሕዝቦች በጋራ ክልል ሊመሰርቱ  እንደሚችሉና መስርተው በሚተዳደሩበት ክልልም ያሉ የውስጥ ጉዳያቸውን በራሳቸው ማየት እንደሚችሉ ሕገመንግስታዊ መሠረት መኖሩን፤ ክልል መስርተው በጋራ በሚኖሩ ሕዝቦች ውስጥ የራሳችንን ክልል እንመሰርታለን ወይም እንገነጠላለን የሚሉ ክፍሎች ምን ዓይነት መስፈርት ማሟላት /ፕሮሲጀር መከተል/ እንደሚገባቸውም ህገመንግስቱ በዝርዝር ማስቀመጡና የክልሎችን የውስጥ ጉዳዮች በተመለከተ ግን ክልሎች እራሳቸው እየፈቱ የሚሄዱበት አግባብ መኖሩን ጠቅሰው፣ ክልሉ በሕዝብ በተመረጡ አካላት የሚተዳደር እስከሆነና ሕዝቡና የመረጠውን አካላት ይህ ይጎለኛል ይስተካከልልኝ ብሎ እስከጠየቀ ድረስ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ ብያኔ የመስጠት ሀላፊነት ያለበት ክልሉ በመሆኑ የማንነነት ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ጉዳዩን አይቶ ተገቢ  ውሳኔ መስጠት ያለበት የክልሉ ም/ቤት ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

በማያያዝም በሕዝብ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በአንድ በኩል በተወካዮች አማካኝነት ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚወሰኑበት አካሂድ መኖሩና በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ በቀጥታ

ድምፅ በመስጠት የሚሳተፉበት አሰራር ያለ ቢሆንም ማንነትን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎች ግን ምላሽ ማግኘት ያለባቸው በህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ነው? ወይስ በወኪሎቹ? የሚለው በሕገመንግስቱ ላይ በግልጽ አለመቀመጡን፤ የማንነት ጥያቄ ሲነሳ የመወሰን ስልጣን ያለው የክልሉ ምክር ቤት ነው እስከተባለ ድረስ በተወካዮች በኩል እንዲወሰን ማድረጉ ችግር እንደሌለው፣ ነገር ግን በተወካዮች አማካይነት ማሰወሰኑ የሕዝቦችን ጥቅምና ፍላጎት ሊጎዳ ይችላል የሚባል ከሆነም እንደገና አይቶ ማስተካከል ያለበት የክልሉ ም/ቤት መሆን እነደሚገባው አስረድተዋል፡፡

በመጨረሻም የስልጤን ማንነት በተመለከተ የክልሉ ም/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ ሕዝቡ አምኖ በመረጣቸው ወኪሎቹ አማካኝነት እንዲወሰን ማድረጉ በህገመንግስቱ ላይ ይኽን የሚከለክል ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ሕገመንግስታዊ ስህተት ተሰርቷል ሊያስብለው እንደማይችል፣ ጉዳዩን በሕዝብ ወኪሎች ማስወሰኑ የሕዝቡን ማንነት ከማረጋገጥ አንፃር ጉዳት አድርሷል የሚሉ ጥያቄዎች ከተነሱም የክልሉ ም/ቤት የራሱን አካሄድ እንደገና እንዲመረምር ዕድል ሊሰጠው እንደሚገባው አመልክተዋል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴሬሽን ም/ቤት የሕዝቦች ማንነት መወሰን ያለበት በሕዘብ ውሣኔ ነው ብሎ ለክልሉ ውሳኔ ማስተላለፍ ተገቢ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ሕዝቡ ጥያቄዬ በአግባቡ አልተመለሰም እንደገና ይታይልኝ ብሎ ያቀረበውን ጉዳይ

የክልሉ ም/ቤት እንደገና እንዲመረምረው ተሰጥቶት በምላሹ ውሳኔው አግባብነት ያለውና ሕገመንግስቱን የተከተለ በመሆኑ በድጋሜ ተመልሼ አላይም የሚል ከሆነ የፌዴሬሽን ም/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ ውሳኔ ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከዚያም ከብርት ወ/ሮ አረጋሽ ሚደቅሣ የቤቱ አካሄድ በቅድሚያ ሕገመንግስታዊ ድጋፍ ይሰጣሉ በሚል በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አካሔድና በክልሎችና ህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረቡትን አንቀጾች ማለትም አንቀድ 39/4/ 39/5// 47/3/ 52/ሀ/ እና 62/3/ ትክክለኛነት ላይ ከተነጋገረ በኋላ የስልጤ ጥያቄ እንዴት ታይቷል ወደ ሚለው አጀንዳ ቢኬድ ከአንድ አጠቃላይ ሀሳብ ላይ መድረስ ያስችላል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም ክቡር አቶ ፀጋዬ ማሞ የማንነት ጥያቄ ሲነሳ መመለስ ያለበት እንዴት ነው? በሚለው አጀንዳ ላይ ለመነጋገር የስልጤን ጉዳይ በአብነት ማንሳቱ በአካሄድ ላይ ችግር ያስከትላል የሚል እምነት እንደሌላቸው፣ የፌዴሬሽን ም/ቤት በአንድ በኩል ክልሎች የውስጥ ጉዳያቸውን በራሳቸው መፍታት አለባቸው እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የማንነት ጥያቄ ሲነሳ መፈታት ያለበት በዚህ መንገድ ነው በማለት ለክልሎች ማስተላለፍ ውሣኔውን የሚጋጭ አያደርገውም ወይ? የማንነት ጥያቄ ለማንኛውም መብቶች ምንጭ ነው እየተባለ ጉዳዩን ለመወሰን ግን በዚህ መንገድ

ተከተሉ በማለትና የ6 ወር የጊዜ ገደብ መስጠቱ ከጉዳዩ ክብደት አንጻር ሲታይ አስቸጋሪ አይሆንም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያቀረቡ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ ማንነቱ ተከብሮና በጋራ ተባብሮና ተማምኖ በመኖር መብቱ ላይ ተቃውሞ ያለው የም/ቤት አባል እንደሌለ ቢታወቅም፤ እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች አንዳንድ ጊዜ ወደ ጥቃቅን ጉዳዮች በማምራት መጨረሻ ወደሌለውና ምላሽ ወደማይገኝለት ሁኔታ ሊያስገቡ ስለሚችሉ የቤቱ አካሄድና ውሣኔ ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በማስከተልም ክቡር አቶ ሀሰን ሺፋ የማንነት ጥያቄን አስመልክቶ የሚወሰነው በማንና እንዴት ነው? የሚለውን እንዲሁም በክልልና ጥያቄውን ባቀረበው አካል መካከል ለሚፈጠረው አለመግባባት የፌዴሬሽን ም/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል ሲባል ምን ማለት ነው? የሚለው አከራካሪ ነጥብ መሆኑን ለምሳሌ አንድ ብሔረሰብ ባቀረበው የማንነት ጥያቄ ላይ ክልሉ ማንነትህ ይህ አይደለም ያለውን የፌዴሬሽን ምክር ቤት በራሱ አካሄድ በቀጥታ መርምሮ ብሔረሰቡ ያለው ትክክል ነው ብሎ ይወስናል ወይስ በዚህ አካሄድ ስላልመረመርከው እንደገና ተመልከተው በሚል ክልሉ እራሱ እንዲፈታው ያደርጋል? የሚለው ግልጽ መሆን እንዳለበት በሕገመንግስቱ ላይ የተቀመጠው ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ ከሚለው በተጨማሪ በውሳኔ ሀሳቡ ውስጥ ‹‹ማህበረሰብ›› በሚል የተካተተው ቃል ትርጉም ምንድን ነው? ማህበረሰብና ብሔረሰብ

ልዩነት አላቸው የላቸውም የሚለው በግልፅ መቀመጥ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በማያያዝም ማንኛውም አካልም ሆነ ግለሰብ ሕገ መንግስቱ ተጥሷል ብሎ በማንኛውም ጊዜ ለሚያቀርበው ጥያቄ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተቀብሎ ማስተናገድ የሚገባው መሆኑና ም/ቤቱም የማንነት ጥያቄን ለመወሰን የሚያስችሉ መርሆዎችን በቅድሚያ በማስቀመጥ ከዚያ በኋላ የስልጤን ጉዳይ ክልሉ መመልከቱ አግባብ ነው ወይስ አደለም የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ከዚያም ክቡር አቶ ከማል በድሪ ከቤቱ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ የማንነት ጥያቄ ሲነሳ ምላሽ የመስጠት ስልጣን ያለው ክልሉ ለመሆኑ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔውም ሆነ የክልሎችና የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መግለፁንና የፌዴሬሽን ም/ቤት ግን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 62/3 መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን፣ ነገር ግን የፌዴሬሽን ም/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል ሲባል በይግባኝ ከሚታየው የፍርድ ቤት ውሳኔ ጋር አንድ አለመሆኑ፣ ይኸውም የሕገ መንግስት ትርጉምን ስራ ላይ የማዋል ጉዳይ የፖለቲካ ሂደትን የሚመለከት በመሆኑ እንደ ጉዳዩ ልዩ ጠባይ ሊለያይ እንደሚችል፣ ስለዚህ የፌዴሬሽን ም/ቤት የማንነት ጉዳይ በነዚህ መስፈርቶች አማካኝነት ነው ውሳኔ ማግኘት ያለበት ብሎ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ክልሉ ካልሄደበትና አቤቱታ ከቀረበለት

የክልሉ አካሄድ ትክክል እንዳልሆነ ገልጾ እንደገና እንዲሄድበት ውሣኔ ያስተላልፋል እንጂ የፌዴሽን ም/ቤት በምንም መልኩ ሕዝበ ውሳኔ የማያካሂድ ወይም የማያስፈጽም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመቀጠልም የማንነት ጥያቄን ለመወሰን የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ችግር አይፈጥርም ወይ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ምንም እንኳን የጊዜ ገደብን ያስቀመጠው የክልሎችና የህገ መንግስት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በመሆኑ የማይመለከታቸው ቢሆንም በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም በኩል በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የጊዜ ገደብ ቀርቦ እንደነበርና ይህ ግን ሕገ መንግስቱን ከመተርጎም አልፎ ሕግ ወደማውጣት የሚወስድ ነው በሚል አጣሪ ጉባኤው አይመለከተኝም ብሎ ማለፉን፣ ነገር ግን ማንነትን ለመወሰን ጥናት የሚካሄድበትና ሕዝበ ውሣኔም የሚዘጋጅበት ከሆነ የቀረበውን የ 6 ወር የጊዜ ገደብ በቂ አይደም ብሎ ቤቱ ሊወሰን እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

በማያያዝም የስልጤ ጉዳይ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ለምን ይቀርባል ለሚለው እንኳንስ አንድ ቡድን አንድ ግለሰብ እንኳን ቢሆን ሕገመንግስታዊ መብቴ በትክክል አልታየልኝም ብሎ ለም/ቤቱ ካቀረበ አቤቱታው የግድ መታየት ያለበት መሆኑንና በዚህ መሠረት አንድ ሕዝብ ብሔር ብሔርሰብ ነኝ ብሎ ለሚያቀርበው ጥያቄ ሕገ መንግስቱ እንዴት ሊያስተናግደው እንደሚገባ እልባት ላይ ከተደረሰ የስልጤ ጥያቄ እንኳንም ተነሳ ሊያስብል እንደሚችል፣ ማህበረሰብ የሚለውን ቃል ትርጉም በተመለከተም

የሕብረተሰብ ክፍል /a group of people/ የሚለውን ለመመልከት እንጂ ቴክኒካል ትርጉም ኑሮት ማህበረሰብ ማለት ይህ ነው ብሔረሰብ ማለት ደግሞ ይህ ነው በሚል በጥናት የተቀመጠ አለመሆኑን፣ ስለዚህ ስልጤ ብሔረሰብ ነው ወይም አይደለም የሚል ጥያቄ ቀርቦ እያለ የስልጤ ብሔረሰብ በሚል መጥራቱ ጥያቄ ላይ ያለን ጉዳይ እንደተወሰነ አድርጎ ያስቆጥራል ከሚል ስሜት የመነጨ እንደሚመስላቸው አስረድተዋል፡፡

ከዚህም ክቡር አቶ ሀሰን ኢብራሂም የማንነት ጥያቄን ለመወሰን የመጀመሪያ ስልጣን ያለው ክልሉ መሆኑንና የፌዴሬሽን ም/ቤትም በአንቀድ 62/3/ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል በማለቱ ላይ ቤቱ በቅድሚያ አንድ አቋም ላይ መድረስ እንደሚገባው፣ ከዚያም የማንነት ጥያቄን ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? በሚለው ላይ በመነጋገር ወደ ስልጤ ጉዳይ መግባቱ ተገቢ እንደሚመስላቸው አመልክተው፣ አንድ የሕብረተሰብ ክፍል ለመገንጠልም ሆነ የራሱን ክልል ለመመስረት በቅድሚያ የማንነቱ ጥያቄ ሊረጋገጥለት የሚገባ በመሆኑ የማንነት ጥያቄ የሁሉም መብቶች መሠረት ነው ለማለት እንደሚያስደፍር፣ በመሆኑም ይህ ጉዳይ በሕዝበ ውሳኔ ይለቅ እንኳን ቢባል በቅድሚያ የመስፈርቶቹ መሟላት መረጋገጥ እንዳለበትና ለዚህም የሚጠየቀው የጊዜ ገደብ ከጥናቱ ስፋትና ጥልቀት ጋር ተገናዝቦ መወሰን እንደሚገባው፣ ማህበረሰብ የሚለው ቃል ትርጉም በተመለከተም በሕገመንግስቱ ላይ ብሔር ብሔረሰብና ህዝብ በሚል የሰፈሩትን ቃላት

መጠቀሙ ጥያቄው ምላሽ ያላገኘለት ጉዳይ እውቅና እንደመስጠት ያስቆጥራል ከሚል ስሜት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በማያያዝም ማንነትን አስመልክቶ ለሚነሱ ጥያቄዎች በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አጠቃላይ መስፈርት በማስቀመጥ የስልጤን ጉዳይ መመልከቱ ተገቢ እንደሚመስላቸውና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልም የስልጤን ጉዳይ አስመልክቶ የወሰነውን ውሣኔ ከመስፈርቶቹ በመነሳት አካሄዱን እንደገና እንዲመለከተው ዕድል ቢሰጠው፣ ያለዚያም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የክልሉን የውሣኔ አካሄድ በመመርመር የውሣኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ቢደረግ የተሻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም ክቡር አቶ አህመድ ሰይድ ‹‹ማህበረሰብ›› የሚለውን ቃል ትርጉም በተመለከተ ማንኛውም የሕብረተሰቡ ክፍል ብሄር ብሔረሰብና ሕዝብ የሚለውን መስፈርት ቢያሟላም ባያሟላም ማህበረሰብ / a group of people / ሊባል ስለሚችል በውሣኔ ሀሳቡ ላይ የተቀመጠውም በዚህ ትርጉም መሆኑን፣ የማንነት ጥያቄ ለሁሉም ምንጭ ትልቅ መሆኑ የሚታመንበት እንደሆነ ጠቅሰው ማንነትን ለመወሰን የተቀመጠው የጊዜ ገደብም የመገንጠልና የክልል ምሥረታ ጥያቄን ለመወሰን ከሚጠይቀው ጊዜ የበለጠ ሊሆን አይችልም ከሚል መነሻ እንጂ ቤቱ የተቀመጠው የ 6 ወር ጊዜ ያንሳል ወይም ይበዛል የሚል ከሆነ ሊያሻሽለው እንደሚችል ጠቁመው፣ የስልጤ ጉዳይን

በተመለከተም ምንም እንኳ ጉዳዩ ለፌዴሬሽን ም/ቤት የቀረበ ቢሆንም የክልሉ የውስጥ ጉዳይ በመሆኑ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ለመሰራቱ ክልሉ እንደገና የማየት ዕድል ቢሰጠው የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

ከዚያም ክብርት ወ/ሮ አልማዝ መኮ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ በማንነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ መስጠት ያለበት ማነው የሚለውን በተመለከተ በቤቱ ውስጥ ልዩነት አለመኖሩን፣ ይኸውም የማንነት ጥያቄ የክልሎች የውስጥ ጉዳይ በመሆኑ ክልሎች መርምረው የመወሰን ስልጣን እንዳላቸውና በውሳኔ ሰጪውና በጥያቄ አቅራቢው አካል መካከል አለመግባባት ከተፈጠረም በሕገመንግስቱ አንቀፅ 62/3/ መሠረት የፌዴሬሽን ም/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት እንደሚችል ስምምነት ላይ መደረሱን፣ ነገር ግን እንደዚህ አይነት ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ የማየት ሂደትም /የፕሮሲጀር/ ሲሆን ክልሉ አይቶ እንዲያስተካክል ለምን ዕድል አይሰጠውም? የሚል ሀሳብ ከቤቱ መቅረቡንና እዚህ ላይ የሚታየው ሁኔታ ግን በሁለቱ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን ሚዛን የማስጠበቅ ማለትም በአንድ በኩል በክልሎች የውስጥ ጉዳይ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት አለማድረግና በሌላ በኩል ደግሞ በየክልሉ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተገቢው ወቅትና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ መብቶቻቸው ተግባራዊ እንዲሆኑላቸው የማድረግ ሁኔታ እንደሆነ አብራ ርተዋል፡፡

በመቀጠልም የፌዴሬሽን ም/ቤት የክልሎች ወይም የሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መርህ በሥራ ላይ እንዲውል የሚታገል፣ የሕዝቦች ሕገ መንግስታዊ መብቶችም በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይሸራረፉ የመከታተልና የማስተካከል፣ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በተመሳሳይ መልኩ ተፈጻሚ የሚሆን የጋራ መስፈርት የማስቀመጥ ኃላፊነት ያለው መሆኑን፣ የሕዝቦችን የማንነት ጥያቄ ለመወሰን የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ የተፈለገውም በአንድ በኩል የክልሎች መብት ሲጠበቅ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቦች መብት እንዳይሸራረፍ ከመከላከል አንፃር መሆኑን አመልክተው የፌዴሬሽን ም/ቤት ሕገመንግስታዊ ድንጋጌዎችን በቅንጅት ከማስተባበር አንፃር የጊዜ ገደቡን ወስኖ ለክልሎች እንዲወርድ ማድረጉ በክልሎች የሚወሰን ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት እዳልሆነ አስረድተዋል፡፡

በማስከተልም የሕዝቦች መብት በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ አረዳድና በተገቢ የጊዜ ሰሌዳ ምላሽ ያግኝ ብሎ አንድ ዓይነት መስፈርት ማስቀመጡና በጋራ ሆኖ ተግባራዊነታቸውን የመከታተሉ ጉዳይ በክልሎች ላይ የሚያሳድረው ጫና ይኖራል ብለው እደማያምኑ፣ የፌዴሬሽን ም/ቤትም ክልሎችን በዚህ መልኩ የማይደግፍና የሕዝቦች መብትንም ተግባራዊነት በእንደዚህ ዓይነት አግባቦች ተከታትሎ የማያስፈጽም ከሆነ አስፈላጊነቱ እንደማይታያቸው፣ ስለዚህ ቤቱ አንድ ዓይነት መስፈርት መቀመጡን ማየት ያለበት አንዱ አካል በሌላው ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት ወይም የክልሉን የአሠራር ነፃነት ከመገደብ

አንፃር ሳይሆን ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ መታየት እዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

በማያያዝም የማንነት ጥያቄዎችን በጥናት አስደግፎ በተጨባጭ ለማየትና ለመወሰን ምን ያህል የጊዜ ገደብ መቀመጥ ይኖርበታል የሚለው ተጨማሪ ውይይት የሚጠይቅ መሆኑን፣ የጊዜ ሰሌዳው አያስፈልግም የሚባል ከሆነ ግን ችግር ይኖረዋል ብለው እንደሚያምኑ፣ ክልሉ ጉዳዩን በአመቸው ጊዜ መርምሮ ውሣኔ ይስጥ የሚባል ከሆነ የጠያቂውን ሕብረተሰብ ክፍል መብትም መጋፋት እንደሆነ አመልክተው በክልሎችና የህገ መንግሥት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበው የ 6 ወር የጊዜ ገደብ ከጉዳዩ ክብደት አንፃር በቂ አይደለም የሚባል ከሆነ ቤቱ ያመነበትን የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ የሚቻል መሆኑንና ቤቱም ‹‹በፕሮሲጀር›› ጉዳዮች ላይ ብቻ በማተኮር ውይይቱን እንዲቀጥል አሳስበዋል፡፡

በዚህ መሰረት ክቡር አቶ ሀሰን ሺፋ የማንነት ጥያቄን በተመለከተ ወሣኙ ማነው በሚለው ላይ በመጀመሪያ ክልሉ ከዚያም የፌዴሬሽን ም/ቤት ነው የሚለው በአጠቃላይ ሲታይ ትክክል ቢሆንም ከሕገመንግስቱ መንፈስ አንፃር አንድ ብሔረሰብ ስለማንነቱ በበላይነት ውሣኔ መስጠት ያለበት እራሱ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው፣ አንድ ብሔረሰብ የራሱን ክልል እመሠርታለሁ ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ ክልሉ ማድረግ የሚችለው ሂደቱን (ፕሮሲጀሩን) የመከታተል ጉዳይ እንጂ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ በዚህ መንገድ ነው መሄድ የምትችለው ብሎ ሊወስን

እንደማይችል፣ የፌዴሬሽን ም/ቤትም ክልሎች ሕገመንግሥቱን የሚጥስ አካሄድ ሲከተሉ ከሕገመንግስቱ ውጭ ናቸው ብሎ እንዲያስተካክሉ የማድረግ ስልጣን እንዳለው ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም ሕገመንግስቱ የፌዴራል መንግስት አባላትን አስመልክቶ በአንቀፅ 47 ላይ በዝርዝር ያስቀመጠ መሆኑና የአንድ ብሔረሰብ የክልል መመስረት ጥያቄም በብሔረሰቡ ም/ቤት 2/3ኛ ድምፅ ሲረጋገጥ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ም/ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔረሰብ ሕዝበ ውሣኔን ማዘጋጀት እንጂ ማድረግ አለብህ ወይም የለብህም በማለት መወሰን እንደማይችል በአንቀፅ 47/3/ ሀ ና ለ / ላይ በግልፅ መደንገጉን ከጠቀሱ በኋላ በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በኩል የቀረበውን የውሣኔ ሀሳብ የተረዱትም ሕዝቡ የፈለገውን የመወሰን መብት አለው በሚል መልኩ መሆኑንና ጉዳዩን ክልል ይመልከተው ሲባልም ከሕገመንግስቱ አንፃር እንዴት ነው የተከሄደበት ለማለት እንደሆነ ገልፀው፣ የማንነትን ጉዳይ ለመወሰን ብሔር ወይም ብሔረሰብ መሆን ብቻ ሣይሆን በ 2/3ኛ ድምፅ ለመደገፍም ም/ቤት መኖርን የሚጠይቅ መሆኑንና ከዚህ አንፃርም የስልጤን ጉዳይ ለመወሰን ሕዝበ ውሣኔ ይደረግ እንኳን ቢባል የስልጤ ም/ቤት የሚባል ስለሌለ 2/3ኛውን ድምፅ የሚሰጠው የክልሉ ም/ቤት ነው ወይስ ማነው በማለት ጠይቀዋል፡፡

ቀጥለውም የስልጤን የማንነት ጥያቄ ለመፍታት ክልሉ በተወካዮች አማካኝነት በተሰጠው ድምፅ መሠረት እልባት የሰጠበት ሁኔታ እንዳለ ገልፀው ከዚህ አንፃር የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔው የማንነት ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ መፍትሔ ማግኘት እንዳለበት ሲወስን ክልሉ ጥያቄውን በዚሁ መንገድ ሊፈታ እንደሚችል የሚጠቁም በመሆኑ ቀድም ሲል የተሰጠው ውሳኔ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የተወሰነ መሆኑን ክልሉ ሊያረጋግጥ የሚችል እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

አያይዘውም ወደፊት መዳበር የሚገባቸው ሀሳቦች እንደሚኖሩና በአሁኑ ሁኔታ ግን ክልሉ እንደገና ጊዜ ወስዶ እንዲያየውና እንዲፈታው ማድረግ፣ ካልፈታው ግን ጥያቄው ተመልሶ ስለሚመጣ ጥያቄውን በማየት ረገድ ስልጣኑ የክልሉ ወይም የፌዴሬሽን ም/ቤት ስለሚሆን አከራካሪ እንዳይሆን በግልፅ መቀመጥ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰብ ምንነት በሕገመንግስቱ አንቀፅ 39/5 መሠረት "ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ" የሚለውን የሚያመለክት ስለሆነ ማህበረሰብ ለሚለው ቃል በአጣሪ ጉባዔው የውሳኔ ሃሳብ ላይ የተሰጠው ትርጉም ከሕገመንግስቱ ጋር እንዳልተጣጣመ አመልክተዋል፡፡

ክቡር አቶ አብዱልዋሴ ዮሴፍ የመገንጠል ጥያቄን፣ የራስን ክልል የመመስረት ሁኔታንና አንድ ህዝብ የማንነት ጥያቄ አቅርቦ ብሔር፣ ብሔረሰብ መሆኑ ታውቆለት በተወሰነ ክልል ግዛት ውስጥ

ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር የሚያስችለውን መብት ሕገመንግስቱ እንደሚያስተናግድ ካስገነዘቡ በኋላ አሁን ግን የተነሳው የክልል ምስረታ ወይም የመገንጠል ጥያቄ ሳይሆን በአንድ በተወሰነ ክልል ውስጥ አንድ ሕዝብ ማንነቱ ታውቆለት ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን ሥርዓት ለመዘርጋት ምን ያህል ጊዜ ያስፈልገዋል? የሚለው ጥያቄ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ሕገመንግስቱ የማንነት ጥያቄን በተመለከተ ካስቀመጣቸው አራት መስፈርቶች ውስጥም ቋንቋና መልክዓምድር ተጨባጭ ሁኔታዎች /objective condition/ መሆናቸውን፣ እነዚህም ገና ወደፊት የሚጠኑ ሳይሆኑ ተጠንተው በመረጃ ደረጃ ተቀምጠዋል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀው የቀረ ነገር ቢኖር ግን የሕዝቡ ባህል ምን ይመስላል? የሚለው እንደሆነና ይህንንም የታሪክ አጥኚዎች ያጠኑት ወይም ያላጠኑት ክፍል ሊኖር እንደሚችል በመጠቆም ዋናው ነገር የሕዝቡን ሥነ ልቦናዊ ማንነት ለማወቅ ደግሞ ወሳኙ ራሱ ሕዝቡ በመሆኑ ይህን ጥያቄ ለመፍታት ሕዘበ ውሳኔ ለማደራጀት ስድስት ወር ይበቃል ወይስ አይበቃም? የሚለውን አካሄድ ማየት እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡

ከዚያም ክቡር አቶ ዮሴፍ ኩማሎ በክልሎች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የለብንም በሚል የቀረበው ሃሳብ ትክክል እንዳልሆነ፣ የፌዴሬሽን ም/ቤት ኃላፊነትና ተግባር በሕገመንግስቱ መቀመጡን በማስገንዘብ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች

ብሔራዊ ክልል የሰጠውን ውሳኔ በመቀየር ጣልቃ መግባት ይሆናል የሚለው አመለካከት ትክክለኛ አካሄድ ስላልሆነ መሰረዝ እንዳለበት ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ ኢያይዘውም የራሱን ማንነት የሚወስነው ራሱ ግለሰቡ ስለሆነ አንድ ሰው ሲዳማ ነኝ ሲል ሌላው ተነስቶ የለም ሃድያ ነህ ቢለው ተቀባይነት እንደሌለው ጠቁመው ከዚህ አንፃር የክልሉ ም/ቤት በስልጤ ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ የአካሄድ ስህተት ካለበት በሕገመንግስቱ በተቀመጠው መሰረት በትክክል እንዲራመድ ጥያቄውን እንደገና ወደ ክልሉ ም/ቤት መመለስ እንደሚሻል የፌዴሬሽን ም/ቤትም ጥያቄውን መሠረት በማድረግ የሕገ መንግሰቱ መስፈርት ምን እንደሚል በመመርመር የማንነት ጥያቄ እንዴት ሊፈታ እንደሚችል መሠረታዊ መስፈርቶችን ማስቀመጥ እንደሚኖርበት አመልክተዋል፡፡

በማያያዝም በሶስት ሰውም ይሁን በአንድ ሰው የማንነት ጥያቄ ከተነሳ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ ሳይሆን ጊዜ በመውሰድ በጥንቃቄ ማየት እንደሚያስፈልግ፣ ስልጤን በተመለከተም የፌዴሬሽን ም/ቤት ዛሬ የሚወስነው ጉዳይ ሳይሆን የክልሉ ም/ቤት የሰጠው ውሳኔም ሕገመንግስቱን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አጣርቶ ማየትና አለማየቱን በበኩላቸው የሚያውቁት ጉዳይ እንደሌለ አመልክተዋል፡፡

አክለውም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የክልሉ ውሳኔ እንዴት እንደሆነ በጥልቀት አልመረመርኩም የሚል ከሆነ ክልሉ

እንደገና ሕገመንግስቱን አገናዝቦ ጉዳዩን እንዲያየው የፌዴሬሽን ም/ቤት በጽሕፈት ቤቱ በኩል ጥያቄ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ጠቁመው የደቡብ ክልል ብዙ ብሔር ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ያካተተ ስለሆነ የስልጤን ጉዳይ ካስተናገድን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር ይከሰታል የሚል አመለካከት ካለ ግን ትክክለኛ አካሄድ እንዳልሆነ፣ ምንጊዜም ሥራው የሚከናወነው በሕገ መንግስቱ ውስጥ የተቀመጡትን መብቶችና ግዴታዎች መሰረት በማድረግ በመሆኑ ሌላውም አካል በግለሰብም ይሁን በቡድን ጥያቄ ካነሳ በሕገመንግስቱ መሰረት እንዴት ይፈታ? የሚለውን ማየቱ የግድ እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡

በመቀጠልም ክብር አቶ ዓለማየሁ ዓለሙ የራሱን ማንነት መወሰን ያለበት ራሱ ሕዝቡ መሆን እንዳለበት ገልፀው እንዴት ይወሰን የሚለው ግን አሁንም ጥያቄ እንደሚያስነሳና የክልል ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕዝቦች ጥያቄ ፍትህዊ ምላሽ የሚያገኙበትን መንገድ በጋራ በመወያየት ማየት እንደሚገባቸውና የማንነት ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜም እንዴት ነው የሚነሳው? ጥያቄውንስ ማን ነው የሚያቀርበው? የክልሉ ምክር ቤትስ እንዴት ነው መሄድ ያለበት? በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ይታይ? የሚሉት ነጥቦች መጤን እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡ አያይዘውም በሕገመንግስት ውስጥ ‹‹በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ የሕዝብ የድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት›› ሲያገኝ የሚለውን መስፈርት ‹‹የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል›› እና ‹‹የራስን ክልል›› የመመስረት ጥያቄ ሲቀርብ

እንዴት ይወሰናል ለሚለው የተቀመጠ መስሎ እንደታያቸው፣ ነገር ግን በአንድ ክልል ውስጥ በመሆን ሕገመንግስቱ ባስቀመጠው መሰረት የእኔም ማንነት በእኔ ውሳኔ ታውቆ መቀመጥ መቻል አለበት ከተባለ በየጊዜው በግለሰብ ወይም በቡድን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሊከሰት ስለሚችል ጉዳዩ እንዴት ሊፈታ እንደሚችልና ጥያቄው በተነሳ ቁጥርም ሕዝበ ውሳኔ እንዴት ማድረግ እንደሚቻል መልስ ያላገኘ መሆኑን ጠቁመው የማንነት ጥያቄው የአብዛኛው ሕዝብ ከሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠቱ የግድ ስለሆነ አካሄዱ እንዴት መሆን እንዳለበትና የመጨረሻው ውሳኔም እንዴት መሰጠት እንደሚኖርበት በቤቱ መታየት እንዳለበት ገልፀዋል ፡፡

ቀጥለውም የማንነት ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ፣ በነፃ ፣ ቀጥተኛና በምስጢራዊ አካሄድ መሆን አለበት ከተባለ ይህንን ለማድረግ መጀመሪያ ጥያቄው የሕዝብ ስለመሆኑ መጠናት እንዳለበት፣ ጥያቄው ከመጣ በኋላም ሕብረተሰቡ እንዲያምንበት ድምጽ የሚሰጥበትን ሁኔታ በመወሰን ረገድም የተግባር እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ጊዜ የሕዝቡ ጥያቄ እንዳይዘገይ ለማድረግና ዝግጅቱም በችኮላ ተከናውኖ ችግር እንዳይፈጥር ለማድረግ በክልሉም ሆነ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰፋ ያለ ጥናት እንደ ሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

ከዚያም ክቡር አቶ ዓለማየሁ ጋሻዬ በበኩላቸው የማንነት ጥያቄን በመወሰን በኩል ለመገንጠልና ለክልል አወቃቀር ከሚሰጠው ጊዜ

ያነሰ እንዲሆን ማድረጉ የራሱ የሆነ ችግር ስለሚኖረውና ለውስጣዊ ችግሮች በጥናት ላይ የተመሰረተ መፍትሔ ለመስጠት እንዲቻል በሕገመንግስቱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ጥያቄዎች በቀረቡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መልስ ማግኘት አለባቸው የሚለውን ለጊዜው መውሰዱ እንደሚሻል ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም ክቡር ዶ/ር ሰለሞን እንቋይ አንድ ብሔር እውቅና ይሰጠኝ ብሎ የሚቀያርበው ማመልከቻ ተቀባይነት የሚኖረው በምን ያህል ሰው ሲቀርብ ነው ለምሳሌ 5 ወይም 6 ሰዎች ሆነው? ወይስ ከብሔሩ ድጋፍ መሰባሰብ ይጠበቅባቸዋል? በማለት ከጠየቁ በኋላ የዚህ ጉዳይ አካሂድ ጠበቅ ያለ ካልሆነ አምስትም ስድስትም ሰው ሲያመለክት ክልሉ የሚያስተናግድ ከሆነ ነገሩ አድካሚ እንደሚሆንና ምንም፣ እንኳን ራሳችን የቻልን ነን ወይም አይደለንም የሚለው በሪፈረንደሙ ድምጽ የሚሰጥበት ቢሆንም ሪፈረንደሙን በማዘጋጀቱ ረገድ ጊዜ የሚወሰድና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ ከዚያ ደረጃ ከመደረሱ በፊት ማመልከቻው ከስንት ሰው መምጣት እንዳለበትና አመልካቾቹ የሕዝቡ ትክክለኛ ወኪሎች መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚቻልበት ሁኔታ በመስፈርቱ ውስጥ መካተት እንደሚኖርት አሳስበዋል፡፡

አክለውም የማንነት ጥያቄ በድንገት በሚቀርብበት ጊዜ ጉዳዩን በጥሞና ለማየትና ለማረጋገጥ እንዲቻል በቂ ጊዜ ማስቀመጡ አስፈላጊ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በማስከተልም ክቡር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ጉዳዩ በክልል ምክር ቤት ስልጣንና በህገ መንግስቱ አንቀድ 62/3 የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል በሚለው መካከል መሆኑን ጠቁመው የሕዝቦች የማንነት ጥያቄ ሲባልና የራስን እድል በራስ መወሰን ሲባል ብዙ ነገሮችን እንደሚያካትት፤ አካሄዱም ክልል ምስረታንና መገንጠልን በተመለከተ በሕገመንግስቱ በግልፅ መቀመጡን ፤ የማንነት ጥያቄን ለማስተናገድ ግን በግልድ የተቀመጠ ነገር ስለሌለ ወደ ክልሉ ቢላክም ክልሉ በተጨባጭ በዚህ መንገድ መሄድ አለብኝ የሚል ሁኔታ ስለሌለው አካሄዱ በግልድ መቀመጥ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

ቀጥለውም የክልል ምስረታን በተመለከተ ጥያቄ ሲቀርብ በህገ መንግስቱ የአንድ አመት የጊዜ ገደብ ስለተቀመጠ በተባለው ጊዜ ካልተፈፀመ ሕገ መንግስቱ ተጣሰ ሊባል እንደሚችልና የማንነት ጥያቄ ግን በስድስት ወር ውስጥ ምላሽ ማግኘት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ ባለመሆኑ በደፈናው ወደ ክልሉ መላኩ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ስለሚሆን ምን ያህል ሕዝብ ሲጠይቅ ሪፈረንደም ሊደረግ እንደሚገባውና ሌሎች ዝርዝር አካሄዶች በግልፅ ቢቀመጡ የተሻለ መሆኑን ጠቁመው ከዚህ አንፃር በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በርካታ ጥያቄዎች የሚነሱበት ሁኔታ በመኖሩ ለጥያቄዎች መሠረታዊ መፍትሄ ለመስጠት የአሰራር ደንቡ በሕገመንግስቱ መቀመጥ አለበት ብለዋል፡፡

ክቡር አቶ ሃሰን ኢብራሂም በበኩላቸው ሕገመንግስቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሉአላዊነት መገለጫ ከመሆኑ አኳያ በሕዝብ ወኪሎች አማካይነት በፀደቀው ሕገ መንግስት መሠረት የማንነት ጥያቄው መስተናገዱን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ማየት እንደሚገባው በመግለጽ አሁን አብዛኛውን ጥያቄ ሊያስነሳ የቻለው የጊዜ ገደብ ሲሆን ጥያቄውም በማን ሲቀርብ የህዝብ ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል አብሮ መታየት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

በማያያዝም የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደተቋቋመ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት አካባቢ በብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ላይ ጥናት ያልተካሄደ እንደሆነ ከዚህ አኳያ የደቡብ ሕዝቦችና ጋምቤላ ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ጥናት እየተካሄደ መሆኑንና ክልሎች በራሳቸው ምሁራን አንዳንድ ጥናቶች በማድረግ ላይ መሆናቸውንና የጊዜ ገደቡን በተመለከተም ጥናት ባልተደረገባቸው ቦታዎች ላይ መስፈርቶቹን በደንብ ለማየት ብዙ ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል አንድ ዓመት የሚለው ቢቀመጥ ጥያቄውን በአግባቡ ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚቻል አመልክተዋል፡፡

አክለውም እያንዳንዱ ክልል ሕገመንግስቱን ተግባራዊ ያደርጋል የሚል እምነት እንዳላቸውና የራስን እድል በራስ ስለመወሰንና ራስን የማስተዳደር መብትን ለመጎናፀፍ ጥያቄውን አቅራቢው ክፍል ራሱ ለመነሻነት ስለጊዜ ገደቡ፤ ስለሕዝቡ ታሪክ ጠቅለል

ያሉ ነጥቦችን ማቅረብ እንደሚኖርበት ጠቁመው ትናንት የጭቆና አካሄድ ተገርስሶ ዛሬ በሕዝቦች ፈቃድ ላይ የተመሰረተች አንዲት ኢትዮጵያ የተመሠረተች ስለሆነ ክልሎችም ይህን ተግባራዊ እንዲያደርጉት የጊዜ ገደቡ እስከ አንድ ዓመት በሚል ቢታይ የተሻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመከጠልም ክቡር አቶ ከማል በድሪ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ የማንነት ጥያቄን ወሳኙ ማን ነው ለሚለው ሕዝቡ ለመሆኑ ጥርጥር እንደሌለ፣ ጥያቄው ለማን ነው የሚቀርበው ከቀረበ በኋላስ እስከ ሕዝበ ውሳኔ ድረስ ያለውን ሂደት የሚያስፈጽመው ማን ነው? ለተባለው ክልሉ የአፈፃፀሚነት ሚና እንዳለው ገልፀው ለምሳሌ የስልጤ ጉዳይ በሕዝበ ውሳኔ ይወሰን ቢባል ስልጤ ማነው? የሚለው የመጀመሪያ ጥያቄ እንደሆነ አፈፃፀሙን በተመለከተም ስልጤዎች ያሉት በጉራጌ ዞን ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ስለሚኖሩ እነዚህ መምረጥ ይችላሉ ወይ? የአመራረጣቸውስ ሁኔታ እንዴት ነው የሚል ዝርዝር ሁኔታ ለክልሉ እንደሚተው፣ ሕዝብ ውሳኔውስ የሚካሄደው ራሱ ክልሉ ባቋቋመው ኮሚሽን ነው ወይስ በምርጫ ቦርዱ አማካኝነት እንዲከናወን ነው የሚፈለገው ለሚለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሁሉም ክልል ተግባራዊ የሚሆን መርህ እንደሚያወጣና ሕዝበ ውሳኔ ሲካሄድም ምን ምን ሁኔታዎች መካተት እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ መቀመጡን አስገንዝበዋል፡፡

በማያያዝም ጥናትን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የግድ ጥናት መደረግ አለበት ወይ? ለምሳሌ በተደረገው ጥናት ራሴን የቻልኩ ሕዝብ ነኝ የሚል ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት አይደለህም ቢባል ወደ ሪፈረንደም መሄዱን እንደማያስቀረው ከገለፁ በኋላ ዝርዝር ጉዳዮችን ለክልሉ መተው ጠቀሚታ እንዳለው፣ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች እውቅና ለመስጠት የግድ ሪፈረንደም ይደረግ ወይም ጥናት ይካሄድ መባል አለበት ወይ? ጥያቄው ሲቀርብም በማያወዛግብ ሁኔታ እንዴት ይፈታል የሚለውን ማስቀመጡ አግባብ እንደሆነ፤ አንድ ህዝብ ራሴን የቻልኩ ነኝ ሲል ሌላው እውቅና አልሰጥም የሚለውን መፍታት የሚቻለው የሕብረተሰቡ አባል በክልሉ አማካኝነት በሕዝብ ውሳኔ ሀሳቡን ሲገልጽ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የጊዜ ገደብን በተመለከተና የማንነት ጥያቄው የሕዝብ ጥያቄ ነው አይደለም? ስንት ሰው እንደጠየቀስ መቀመጥ የለበትም ወይ? ለተባለው ይህን ማድረጉ ሕገመንግስቱን እነደገና መጻፍ ስለሆነና ስልጣኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሆነ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩን በዝርዝር አይቶ የጊዜ ገደብ አለማስቀመጡን ገልጸው ስልጤን በተመለከተ ምን ያል ሰው ነው ጥያቄውን ያቀረበው ለተባለው ጥያቄው በሕዝቡ መቅረቡን ክልሉ ግምት ውስጥ አስገብቶ ውሳኔ የሰጠበት ሁኔታ ስላለ የሕዝብ ጥያቄ ነው ወይ እያሉ እንደገና ወደኋላ መሄዱ አግባብ ስላልሆነ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ በተገባ ቁጥር በሕገመንግስቱ ላይ ንዑስ አንቀድ የማስገባት ሁኔታ እንዳይፈጠር የሚል ስጋት እንዳላቸው፣ ከዚህ

አኳያ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገመንግስቱን የመተርጎም ስልጣን ስላለው ግልጽ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ተርጉሞ መመሪያ ማስቀመጡ አግባብ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ከዚያም ክብርት አፈጉባኤዋ በበኩላቸው የጊዜ ገደብን በተመለከተ በአንድ በኩል እስከ አንድ ዓመት የሚል ገደብ ይቀመጥ የሚል ሃሳብ መቅረቡን በሌላ በኩል ደግሞ አንድ አመት ወይም ስድስት ወር ይሁን ተብሎ የሚወሰን ሳይሆን በጥናት ቢወሰን ይሻላል የሚል እንደሆነ ገልጸው ሌላው ነጥብ ደግሞ የማንነት ጥያቄውን የሚያቀርበው ማነው ለሚለውም የስልጤንም ሆነ የሌላውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል አጠቃላይ መመሪያ እንደሚያስፈልግ፤ የማንነት ጥያቄ በግለሰብም ይቅረብ በቡድን በተወሰነ የድጋፍ ፊርማ ይደገፍ ወይም አይደገፍ የሚለው በሕገመንግስቱ ላይ የተገለጸ ነገር እንደሌለ፣ ነገር ግን እስከአሁን ባለው ግንዛቤ ጥያቄው በግለሰብም ሆነ በቡድን መቅረብ ይችላል የሚል መሆኑን አስገንዝበው ሕገ መንግስቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ባላለበት ሁኔታ ይህ ጉባዔ ተጨማሪ ጊዜ በመውሰድ ቢወያይም ማን ማቅረብ አለበት በሚለው ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንደማይችል አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝበ ውሳኔ ለማካሄድ ጥናት እንደሚያስፈልግ ከቤቱ ሃሳብ መቅረቡን ፤ ለሚቀርበው ጥያቄ ሁሉ ሕዝበ ውሳኔ ይደራጅ ከተባለ ግን ረጅም ጊዜን ስለሚወስድና ከፍተኛ ወጪም የሚጠይቅ ስለሆነ በምን ዓይነት ሁኔታ ይካሄድ የሚለው በጥናት

መመለስ ይኖርበታል የሚል አስተያየት እንዳለና በዚህ ጉዳይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ጥያቄውን ማን ያቅርብ የሚለው በሕገመንግስቱ በግልጽ እስካልተቀመጠ ድረስ በምን አይነት መልኩ ሲቀርብ ሕዝበ ውሳኔ ይደራጃል? በምን መልኩ ሲቀርብ ነው ሕዝበ ውሳኔ ቀረቶ ሌላ ምላሽ የሚሰጠው? የሚለውን ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ስለሚሆን ክልሎች እንደ የራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያደራጁ ቢተውላቸው የሚል አስተያየት ማቅረቡን አስታውሰው ከዚህ አኳያ የተጠቀሱትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ለሁሉም ክልሎች የሚሆን የተወሰነ መመሪያ ይቀመጥ ወይስ ለሌላ ጊዜ ይተላለፍ? ጉዳዩ ዘግይቶስ በዚህ ነገር ላይ የመጨረሻ እልባት ሊሰጥበት ይችላል አይችልም የሚለው አብሮ መታየት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

ቀጥለውም የጊዜ ገደቡን በተመለከተ በሕገ መንግስቱ አንቀድ 47 ላይ ክልል የመመስረት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎችን አልፎ ሕዝበ ውሳኔ ይደራጃል የሚለው ለማንነት ጥያቄም እንደመነሻ ቢወስድ ችግር አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ቤቱ እንዲወያይበት ጠቁመው ጉባኤው ለሻይ እረፍት ተነስቷል፡፡

ከሻይ እረፍት መልስ ውይይቱ የቀጠለ ሲሆን በቅድሚያ ክብርት ወ/ሮ አልማዝ መኮ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤ ቀደም ሲል በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥባቸው መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

በዚህም መሰረት ክቡር  አቶ ሀሰን ሽፋ የማንነት ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ ክልሎች በተመሳሳይ መልኩ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉበትን መሠረታዊ መርሆዎች በማስቀመጥና በአፈፃፀም ረገድ ሊኖሩ የሚገባቸውን አካሄዶች በዝርዝር ለማስቀመጥ ደግሞ ሕገመንግስቱን መሰረት ያደረገ ወርክ ሾፕ በማዘጋጀት ጥናት ማድረጉ የተሻለ መሆኑን ጠቁመው ከዚህ አንፃርም ሕገመንግስቱስ መሻሻል ያስፈልገዋል አያስፈልገውም የሚለውን ማየት እንደሚያስፈልግና የስልጤን ጉዳይ በተመለከተ መሆን የነበረበት የስልጤ የራሱ ምክር ቤት ኖሮት ጥያቄው በምክር ቤቱ ሁለት ሶስተኛ ድምጽ ከተደገፈ በኋላ ወደ ህዝብ መመራት እንዳለበት በማስገንዘብ ይህን ለማድረግ ግን ያለው የጉረጌ ዞን ምክር ቤት እንጂ የስልጤ እንዳልሆነ፣ ባለው ምክር ቤት እንዳይካሄድ ደግሞ ጉራጌ ስለ ስልጤ ምን ብሎ ይወስናል?  የሚለው ክርክር እንደሚያስነሳ ገልጸዋል፡፡

አክለውም በሕገ መንግስቱ መሠረት አንድ ሰው ጥያቄ ካቀረበ መልስ ማግኘት ቢኖርበትም ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ግን የተወሰኑ ሰዎች የማንነት ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ክልሉ ሪፈረንደም ማደራጀት አለበት ወይ?  በሚል ከጠየቁ በኋላ ጉዳዩን በረጋ መንፈስ ማየትና አንድ አይነት መርህ ማስቀመጥ አስፈላጊ መሆኑን በፌዴሬሽን ምክር ቤት ደረጃ የተቀመጠውን መርህ መሠረት በማድረግ ክልሉ ችግሩን እንዲፈታው ማድረጉ የተሻለ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ክቡር አቶ ዓለማየሁ ዓለሙ በበኩላቸው የማንነት ጥያቄውን ማንሳት የሚችለው ማን ነው? ጥያቄውስ ትክክል መሆኑን ክልሉ የሚያረጋግጠው በምን ያህል ጊዜ ነው? የሚለውን ክልሉ ራሱ እንዲያየው ከተደረገ ችግር ሊያስከትከል እንደሚችል ገልፀው ምንአልባት የደቡብ ክልልን በተመለከተ ጥያቄውን የሚያቀርበው ሰው 100 ወይም 500 ሰው፣ የጊዜ ገደቡ ደግሞ ስድስት ወር ወይም አንድ ዓመት ሊባል ቢችልም ጥያቄው የደቡብ ብቻ ካለመሆኑ አኳያ ሌሎች ክልሎችም ጥያቄው ከቀረበ የራሳቸውን አካሂድ ይከተሉ ወደሚለው አካሂድ ስለሚወስድ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጊዜ ወስዶ በደንብ መወያየቱ አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ቀጥለውም የስልጤን ጉዳይ በተመለከተ ምክር ቤቱ እንዳስቀ መጠው ወደ ክልሉ ይመለስና በፊት የሄደበት አቅጣጫ ምን እንደሚመስልና አሁን ምን መደረግ እንዳለበት አይቶ ይመልሰው በሚለው ላይ ብዙም ተቃውሞ እንደሌላቸው፣ ነገር ግን ለምክር ቤቱ ያልቀረቡ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ለእነዚህ ተመሳሳይ ጉዳዮች እልባት ለመስጠት እንዲያስችል ሕግ መቀመጥ ስላለበት የማንነት ጥያቄን ማን ማቅረብ እንደሚችል፣ ከቀረበ በኋላም እውነተኛ የሕዝብ ጥያቄ ለመሆኑ ክልሉ አረጋግጦ እንዴትና በምን ያህል ጊዜ ሕዝበ ውሣኔውን ያመቻቻል የሚለውን የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤት ተባብረው ወርክሾፕ በማዘጋጀትም ሆነ የተለያዩ ባለሙያዎች ሀሳብ የሚሰጡበትን ሁኔታ በመፍጠር በጉዳዩ ላይ

ሰፊ ውይይት ማድረግና ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚገባው አመልክተዋል፡፡

ከዚያም ክብርት አፈጉባኤዋ የማንነት ጥያቄ ከሚሰጠው ምላሽ አንፃር ሲታይም በሩጫ መወሰን እንደሌለበት አስገንዝበው በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህ ውይይት መነሻ የሆነው የስልጤ ጉዳይ ረዥም ጊዜ ከመውሰዱና ውሣኔ ሳያገኝ ተንጠልጥሎ ከመቆየቱ አንፃር ሲታይ አንድ ነገር መባል እንዳለበትና ምክር ቤቱም ኃላፊነቱን መወጣት መቻል እንደሚጠበቅበት ገልጸዋል፡፡

ቀጥለውም በዚህ ዙርያ ላይ የተሟላ ግንዛቤ ወይም አጠቃላይ ሁኔታዎችን ለመመለስ የሚያስችል መመሪያ ጉባኤው እያስቀመጠ ሳይሆን ነገር ግን የብሔር የማንነት ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ ማን ነው የሚወስነው የሚለው ወሳኙ ሕዝብ፣ እንደሆነ ሕዝቡ ውሳኔ እንዲሰጥ የመጀመሪያውን ሚና ከሚጫወቱት የመንግስት አካላት መካከል ዋናው የክልል ምክር ቤት መሆኑን ቤቱ እንዲስማማበት ገልጸዋል፡፡

አስከትለውም የክልል ምክር ቤት ጥያቄውን ካልፈታውስ እንዴት ይታያል ለሚለው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 62/3 መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጉዳዩን አይቶ አካሄዱን እንደሚያስቀምጥ በዚህ መሠረትም የክልል ም/ቤቶች እንዲወስኑ ያደርጋል የሚል እንደተቀመጠ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሕዝቡ ራሱ ስለማንነቱ እንዲወስን የክልል ምክር ቤት በምን ሥርዓት ነው ጉዳዩን መምራት ያለበት ለሚለው ጥያቄ በሪፈረንደም ይደረግ የሚል

መቀመጡን፣ ይህ ማለት ግን ጥያቄው በቀረበ ቁጥር ሁልጊዜ ወደ ሪፈረንደም ይኬዳል ለማለት ሣይሆን ሕዝቡ ማንነቱን እንዲያውቅ ለማድረግ በነፍስ ወከፍ ቀርቦ ስለማንነቱ የሚገልጽበት የሪፈረንደም ስርዓት መመቻቸት እንዳለበት አስገንዝበው፣ ሌሎች መፈታት የሚገባቸው ጉዳዮች ደግሞ የክልሉ ምክር ቤት ግልፅ የሆኑ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሊወስን እንደሚችልና እስከ ሪፈረንደም የሚያስኬዱ መስፈርቶችን መጠቀም እንደሚኖርበት ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም የማንነት ጥያቄን ማቅረብ የሚችለው ማነው ለሚለው በሕገ መንግስቱ የተገለጸ ነገር ካለመኖሩ አንፃር ግልጽ የሆነ አቅጣጫ በማስቀመጥ በኩል ከቤቱ ሃሳብ የተነሣ ሲሆን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕግ አውጪ ስላልሆነ ካለው ኃላፊነት አንፃር ይህን ለማድረግ እንደማይችል፣ አጣሪ ጉባኤውም ተጨማሪ አስተያየት ለማቅረብ እዚያ ድረስ ዘልቆ ለመግባት የሚያስችለው ስልጣን እንደሌለው አስገንዝበው ከዚህ አኳያ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግስት ተርጓሚ አካል በመሆኑና ክልሎች ደግሞ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ እንዳላቸው፣ ስለሆነም የክልሉ ስራ አስፈፃሚ የክልሉን ሕገ መንግስት የመተርጎም ኃላፊነት ስላለው የማንነት ጥያቄንው በማን ሲቀርብ መፍትሔ መስጠት እንደሚችል የክልሉን ሕገመንግስት ተርጉሞ አካሄዶችን መደንገግ እንደሚችል፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚና ደግሞ ክልሉ ሕገመንግስቱን የሚፃረር ዝርዝር ሕግ አውጥቷል የሚል ነገር የመጣ እንደሆነና ከዚህም ተነስቶ ግንዛቤውን እያዳበረ ስለሚሄድ

ለሁሉም ክልል የሚሰራ አንድ ዓይነት መርህ መደንገግ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

ክብርት አፈ ጉባኤዋ ቀጥለውም በሕገመንግስቱ የተቀመጠውን ክልል ለመመስረት ጥያቄ የሚቀርብበትን ጊዜ ማለትም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የሚለውን መነሻ በማድረግ የማንነት ጥያቄ ውሳኔ የሚያገኝበት ጊዜም ከአንድ አመት ባልበለጠ ጊዜ እንዲሆን ማስቀመጡ የሕዝብ የመብት ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ እየተንዛዛ እንዳይሄድና ክልሉም ሆነ ህዝቡ ለጉዳዩ ባስቸኳይ እልባት ሰጥቶ ወደልማት እንዲመለስ ለማድረግ እንደሚረዳ፣ ተጨማሪ ጊዜ በመውሰድ ከየክልሎች ጋር ተወያይተን እንወስን ቢባል እንኳ አንዱ ክልል የሶስት ወር ጊዜ ሌላው የስድስት ወር ሊል ስለሚችል አንድ ዓመት የሚለውን እንደ ከፍተኛ መነሻ ማስቀመጡ ለሁሉም በአማካይ የጊዜ ገደብነት ሊያገለግል ከመቻሉም በላይ ይህ በተግባር ተፈትኖ ያነሰ ሆኖ ከተገኘ ግን የማሻሻል እድሉም ዝግ እንዳልሆነ አስገንዝበዋል፡፡

አያይዘውም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይህን የተወሰነ መመሪያ ይዞ በዚህ መነሻነት አሁን በእንጥልጥል ላይ ላሉ የሕዝብ ጉዳዮችም እልባት እየሰጠ ካልሄደ ጊዜ ጊዜን እየወለደ ችግሩ ሳይፈታ እንዲዘገይ እንደሚያደርገው ገልፀው ባንድ በኩል ክልሉ ራሱን የማስተዳደር መብቱ ሳይነካ፣ በሌላም በኩል የሕዝብ መብትም እንዳይገፋ ሁለቱን በሚያስታረቅ መልኩ ማስቀመጡ የሚጠቅም መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ክቡር አቶ ዘካርያስ ሜጊሶ በበኩላቸው ከላይ የተገለፀው ነገር ትክክል ቢሆንም ክልሉ ይህን ያድርግ የሚለውን አጠቃላይ መመሪያ ለማስቀመጥ የሚያስችግር ነገር እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

ይህንን ሲያብራሩም በሕገመንግስቱ እንደተቀመጠው ጥያቄው የሚቀርበው ምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምፅ ሲደግፈው የሚል ሲሆን የስልጤን ጉዳይ በተመለከተ ችግሩ መኖሩ ባይካድም ጥያቄው ግን በጉራጌ ዞን ምክር ቤት 2/3ኛ ድምፅ የተደገፈ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል ጥያቄውን ማን አነሳው የሚለውን በተመለከተም ጥያቄው የተወሰኑ አካላት ጥያቄ ወይም የብዙሃኑ መሆኑን ክልሉ በራሱ አጥንቶ ሊደርስበት እንደሚችል፣ ስነስርአቱንና የጊዜ ገደቡን በተመለከተም ክልል ምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምጽ ሲቀበለው የሚል በሕገመንግስቱ ቢቀመጥም የስልጢ ጉዳይ ሲታይ ግን ይህን ለማድረግ የራሱ ክልል ምክር ቤት ስለሌለው ሪፈረንደም ለማካሄድም ቢሆን የክልል ምክር ቤቱ ታች ህዝቡ ዘንድ ወርዶ በሚያስቀምጠው መልክ የሚፈፅመው እንደሚሆን፣ ከዚህ አኳያ ክልሉ ልማት ስለሚፈልግ ባጭር ጊዜ ውስጥ ለጥያቄው እልባት ይሰጠዋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን የማይመቸው ከሆነም ሊያራዝመው እንደሚችል፣ በመሆኑም ከፌዴሬሽን ምክር ቤት በ6 ወር ወይም በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ብሎ የማስቀመጡ ጉዳይ ከህገ

መንግሥቱ አንፃር ሕገ መንግስታዊነቱ አከራካሪ እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡

በሌላም በኩል ክቡር አቶ ኡርማሌ ኡጋንዴ የማንኛውም ሕዝብ መብት ዋስትና ሕገመንግስቱ ስለሆነና ሕገመንግስቱን ተግባራዊ በማድረግ ወይም ተግባራዊነቱን በመከታተል በኩል የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከፍተኛ ድርሻ ስላለው አሁን የተቀመጠው አቅጣጫ ትክክል መሆኑን ሕዝቦችም ሕገመንግስቱ ተግባራዊ በማይሆንበት ጊዜ በቡድንም ሆነ በግል ጥያቄ የማቅረብና ምላሽ የማግኘት መብት እንዳላቸው፣ ከዚህ አንፃር የሕዝብ መብቶች እንዳይሸራረፉ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበትን የጊዜ ገደብ አስቀምጦ አፈፃፀሙን መከታተልና ማስተካከያም ካስፈለገ እያስተካከሉ መሄዱ ተገቢነት ያለው ስለሆነ በ1 ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚለው ተገቢ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ቀጥለውም የሕዝብን ሕገመንግስታዊ መብት ተግባራዊ ለማድረግ ከክልሎች ጋርም መወያየት እንደሚያስፈልግና የጋራ ግንዛቤም እንዲኖር ወርክሾፕ በማዘጋጀት ክልሎች ውይይት እንዲያደርጉ ድጋፍ ቢሰጣቸው ጠቃሚ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ቀጥለውም ሕገመንግስቱ የበላይነትን የሚሰጠው ለሕዝቡ በመሆኑ ጊዜውም በሕዝብ መወሰን አለበት የተባለው ትክክል መሆኑን፣ በሕገመንግስቱ በተቀመጠው መስማማት ካልተቻለ ሪፈረንደም ማካሄድ እንደሚያስፈልግ፣ በሌላም በኩል የሁለት ሦስተኛ ድምፅ ድጋፍ የሚያስፈልገው የክልል መዋቅር ወይም ሌላ ነገር ሲጠየቅ

መሆኑን፣ የማንነትን ጥያቄ በተመለከተ ግን በብሔር ብሔረሰቦች መብት ላይ የተወሰነ ቡድንም ቢሆን ጠይቆ በሕገመንግስቱ የተቀመጠውን ካሟላ ተግባራዊ ማድረግ እንጂ የሶስተኛ አካል የሁለት ሦስተኛ ድምፅ እደማያስፈልግ ገልፃዋል፡፡

አያይዘውም ማንነት በተፈጥሮ የሚገኝና በሕገመንግስቱም ዋስትና የተሰጠው ስለሆነ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት፣ ይህን ለማስተካከል ግን ክልሉ የተወሰኑ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ሕዝቦች መብታቸውን ራሳቸው እንዲወስኑ ማድረግ እደሚገባው ገልፀው ክልሎችም በየራሳቸው ያለውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ ድጋፍ ሊደረግላቸው እደሚገባ ግልፀዋል፡፡

በዚህ ሂደት ሕዝቡን ወደተሳሳተ አቅጣጫ የሚመሩ ከተገኙም ክልሉ አጣርቶ ለሕዝቡ በሚጠቅመው መንገድ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ቢጓዝ የበለጠ የሕዝቡን ማንነት እያጠናከረና ትስስሩን እያጎለበተ ሊሄድ እንደሚችል ገልፀው በእለቱ የተቀመጠው አቅጣጫ ሕዝቡንም ሆነ ተመሳሳይ ጥያቄ ያላቸውን ሰዎች እደሚጠቅም ገልፀዋል፡፡

ከዚያም በቅድሚያ በቀረበው ሃሳብ ላይ ተጨማሪ አስተያየቶች ካሉ ቀጥሎ ደግሞ የተቃውሞ ሃሳቦች ካሉ እንዲቀርቡ ክብርት አፈጉባኤዋ መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

በዚህም መሰረት ክቡር አቶ አብዱልዋሴዕ የሱፍ በሰጡት አስተያየት የማንነትን ጥያቄ ማን ያንሳው የሚለው ሲታይ ግለሰቦች ወይም የአንድ ብሔረሰብ አባል የሆኑ ሰዎች ጥያቄ ማንሳት እንደሚችሉ፣በዚህ ጊዜም በቅድሚያ ለክልል ምክር ቤት ማቅረብ እንደሚችሉ፣ ቀጥሎም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ ሁኔታ በሕገመንግስቱ ያልተቀመጠውን ገደብ እናደርጋለን ከተባለ ገደቡ ራሱ እስከምን ድረስ የሚለው እደሚያከራክር፣ ለምሳሌ ጥያቄውን ከሕዝቡ መሃል አንድ መቶኛው ወይም አንድሺኛው ደገፈው የሚለው እንደሚያከራክር፣ በመሆኑም ጥያቄው የሕዝብ ጥያቄ መሆኑን ክልሉ እስከተገነዘበ ድረስ በቡድን፣ በሕዝብ ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ቀርቦ መስተናገድ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

የጊዜ ገደቡን በተመለከተም ምንም እንኳ በ6 ወር ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥመጨረስ ይቻላል የሚል አስተያየት ቢኖርም ክልሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጊዜ ስለሚያስፈልገው ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ የሚለውን እንደሚደግፉት አመልክተዋል፡፡

በሌላም በኩል አንድ የማንነት ጥያቄ ለክልል ምክር ቤት ቀርቦ ክልሉ መፍታት ባለመቻሉ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ከቀረበ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አንድ እልባት መስጠት እንደሚኖርበት፣ ከዚህ አኳያ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የቀረበውን የስልጤ ማንነት ጥያቄ በተመለከተ ምክር ቤቱ ከቀረቡለት መረጃዎች አኳያ አገናዝቦ የተጓደሉ ነገሮች ካሉ እንዲያሟላ ለክልሉ ከተወሰኑ መመሪያዎችና የጊዜ ገደብ ጋር መላኩ አግባብነት ያለውና

ለችግሩ እልባት የሚሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ ለወደፊቱም አንድ የአካሄድ ሥርዓት ማስቀመጥ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

በዚሁ ጊዜም ክቡር አቶ ጨንገሬ ፅላ የህዝቦች መብት ያለገደብ የመከበሩ ጉዳይ በሕገመንግስቱ የተቀመጠውን አካሄድ ተከትሎ መፈፀም እንዳለበት፣ ከዚህ አኳያ ጉዳዩን ጥያቄ የተነሣበት ክልል ይመልከተው የሚለውና የማንነት ጥያቄ በአንድም ሆነ ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ሲቀርብ መስተናገድ አለበት የሚለው ትክክል መሆኑን ገልፀው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መልኩ መወሰኑም ትክክል ነው ብለዋል፡፡

አያያዘውም የስልጤ የማንነት ጥያቄ ከቀረበ የተወሰኑ ጊዜያት ስላለፉ ይህንና በሕገመንግስቱ የተቀመጠውን መርሆ ከግምት ውስጥ በማስገባት ክልሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት የተባለው ትክክል ሲሆን የፌዴሬሽን ምክር ቤቱም በራሱ በኩል የጉዳዩን አፈፃፀም መከታተል እንዳለበት፣ ውሳኔውም በሕገመንግሥቱ በተቀመጠው መሰረት በሕዝብ ውሳኔ ቢያልፍ የማያከራክር፣ ተገቢና ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

ከዚያም ክብርት አፈጉባኤዋ ጉዳዩን በተመለከተ የሚነሳ የተቃውሞ ሃሳብ ካለ እንዲቀርብ መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

በዚህም መሠረት ክቡር አቶ ሀሰን ሽፋ በሰጡት አስተያየት ቀደም ሲል በተሰጡት አስተያየቶች የማንነት ጥያቄውን የሆነ ሰው

ካቀረበው ወዲያውኑ መታየት አለበት የሚል ሃሳብ መቅረቡን አውስተው ይህ አስተያየት ግን ቀደም ሲል ቤቱ ከተነጋገረበትና በሕገ መንግስቱ ከተቀመጠው ማለትም አንድ ጥያቄ ሲቀርብ በብሔር ብሔረሰቡ ወይም ህዝቡ ህግ አውጪ ምክር ቤት የ2/3ኛ ድምፅ ድጋፍ ማግኘት እንዳለበት ከተገለፀው ጋር ስለሚቃረን እንደማይደግፉት ጠቁመው ከሁለቱ የትኛውን ቤቱ እየተቀበለ እንደሆነ እንዲብራራ ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በተመለከተም ክብርት አፈጉባኤዋ ሲያብራሩ ጥያቄው ሲቀርብ የብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕግ አውጪ ምክር ቤት 2/3ኛ ድምፅ ድጋፍ ማግኘት አለበት የሚለው በግልፅ በሕገመንግስቱ የተደነገገና ክልሉም ይህንን ተገንዝቦ በዚያው አግባብ እንደሚፈጽማቸው ስለሚታመን በዝርዝር የሚገባበት ጉዳይ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

ቀጥለውም አሁን ግልፅ ያልሆነው ማንነትን በተመለከተ የፓለቲካ ፓርቲዎች የሚኖራቸው ሚና ጥያቄ ማቅረብን በተመለከተ ጥያቄ የማቅረብ ብቻ ነው ወይስ ሕዝቡን ወክለው መወሰን ይችላሉ የሚለው መሆኑን ጠቁመው ጥያቄ ማቅረብና መወሰን የተለያዩ ነገሮች ሆነው ሳለ ሁለቱን አንድ አድርጎ የማየት ችግር እንደሚታይ ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል የማንነት ጥያቄው የጥቂት ስልጣን ፈላጊዎች ነው ወይስ የሕዝብ የሚለው ጉዳይ ባሁኑ ሰዓት ገና ያልለየ እንደሆነ ክብርት አፈጉባኤዋ ገልፀው በሕገመንግስቱ የተቀመጠው ግን

ገደብ እንደሌለው፣ ጥያቄውን ማንም ያቅርበው ማን የሕዝብ የመብት ጥያቄ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ሕገመንግስቱን ተከትሎ መወሰን እንዳለበት መቀመጡን፣ ጥያቄው የጥቂት ሥልጣን ፈላጊዎች ወይም የሕዝቡ መሆኑ እየለየ የሚመጣው ግን ጉዳዩን ለመፍታት በምንከተለው አካሄድ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ነው ካሉ በኃላ ሕዝቡ ውሳኔ ሲሰጥም የሕዝብ የማንነት ጥያቄ የመጨረሻ እልባት ሊያገኝ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የስልጤ የማንነት ጥያቄ ሲታይ ከሕዝቡ መሃል ስልጤ እንጂ ጉራጌ አይደለሁም የሚል የመኖሩን ያህል ቤተጉራጌ ነኝ የሚልም ሊኖር እንደሚችልና ውጤቱ የሚታወቀው ግን እያንዳንዱ ግልሰብ ስለማንነቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሆኑን፣ በጥያቄ አቀራረብም ላይ የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማራመድ ሲባል ሊቀርብ እንደሚችል የታወቀ ሲሆን ይህን ለመከላከል ሲባል ግን የሕዝብ መብት ታፍኖ እንዳይቀር ህዝቡን እያወያዩ በመሄድና በመጨረሻም ድምፅ በመስጠት ጉዳዩን ለመወሰን ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ፣ ይህ ሂደትም አድካሚ ስራ መጠየቁ እንደማያጠራጥር፣ይህ ሳይደረግ ከወዲሁ አውቆ ያልሆነውን አዝማሚያ ማሳየት ተገቢ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

በዚሁ ጊዜም ክቡር አቶ አለማየሁ ዓለሙ ክልሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚል ሲቀርብ የስልጤ ጉዳይ ቀደም ብሎ ሲታይ የቆየ በመሆኑ የጊዜ ገደቡ እሱን ጨምሮ ነው ወይስ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቢነሱ ለእነሱም የሚሆን አካሄድ እንዲቀመጥ

ነው የተፈለገው በማለት ጠይቀው አሁን ለማየት የተፈለገው አጠቃላይ አካሄድ ለማስቀመጥ ነው የሚል ምላሽ ከክብርት አፈጉባኤዋ ተሰጥቷል፡፡

አቶ አለማየሁም ከዚህ በመነሳት አንድ አጠቃላይ አካሄድ ለማስቀመጥ የሚፈለግ ከሆነ ጥያቄውን ማን ማቅረብ እንዳለበት፣ ጥያቄው ከቀረበ በኋላም ክልሉ እንዴት ሕዝበ ውሳኔ መስጠት አለበት የሚሉትንና የመሳሰሉትን ነገሮች መጨረስ ያለበት ክልሉ እንጂ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከዚህ ወስኖ እንደሕግ ገደብ የማስቀመጥ ኃላፊነት አለው ወይ የሚለውም ጥያቄ ስለሚነሳ ከዚህ ሳይወሰን ክልሉ የሕዝቡን ጥያቄ ሊመልስ በሚችል መንገድ ማስተናገድ አለበት የሚል ሃሳብ በቤቱ እየተንሸራሸረ እንደሚመስላቸው ጠቁመዋል፡፡ አያይዘውም ጉዳዩ ከላይ እንደተገለጸው ከሆነ የማንነት ጥያቄ ሲቀርብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ማግኘት አለበት ብሎ ቤቱ ማስቀመጡ ምክር ቤቱ የሕግ ትርጉም እየሰጠ ነው ወይስ አዲስ ሕግ እየጨመረ ነው የሚል ጥያቄም እንደሚፈጥር በመጠቆም ማብራሪያ እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ለዚህም የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀመንበር ክቡር አቶ ከማል በድሪ በሰጡት ምላሽ የማንነት ጥያቄው ሲቀርብ የብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምፅ ከደገፈው እንደሚስተናገድ ቀደም ሲል ከቤቱ የቀረበው የሚለው ሃሳብ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 47/3/ የተቀመጠውን ክልልን

ስለመመስረት የተገለፀውን በመከተል እንደሆነ ጠቂመው ጉዳዩ በሕዝበ ውሳኔ እንዲወሰን ተደርጎ ህዝቡ 50+1 በሆነ ድምጽ ከወሰነ በኃላ ይህ ውሳኔው በመጨረሻ በመረጣቸው ወኪሎች አማካኝነት እንዲፀድቅ ተልኮ 2/3ኛ የድጋፍ ድምጽ ሳያገኝ ቢቀር መልሶ የሕዝቡን መብት መንፈግ እንደሚሆን፣ ይህ ከሆነ ደግሞ ሪፈረንደም ሳያስፈልግ ከመጀመሪያው ክልሉ ራሱ አይወሰነውም ነበር ወይ የሚል ጥያቄ እንደሚያስነሳ አመልክተዋል፡፡

በሌላም በኩል ማንነቴ ይታወቅልኝ ብሎ ጥያቄ የሚያቀርብ አካል ገና የክልልም ሆነ የዞን ወይም ሌላ ምክር ቤት ስለሌው ምክር ቤት በሌለበት ሁኔታ የብሔረሰቡ የክልል ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምጽ ሊያፀድቅለት ይገባል ማለቱ የተፈቀደለትን ነገር በእጅ አዙር መከልከል እንደሚሆን፣ ከዚህ አኳያ ስልጤ ሶስት ወረዳ ያለው ሲሆን እነዚህ ወረዳዎች ባንድ ላይ ተሰባስበው ይወስናሉ ወይስ በተለያየ የሚለው ራሱ የሚያነጋግር መሆኑን፣ በተለያየ ይወስኑት ቢባል እንኳ በሁለት ወረዳዎች በእያንዳንዳቸው 1/3ኛ ድምጽ ቢያገኙ ይሄ ውጤት ተደምሮ 2/3ኛ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩን፣ ወይም በሁሉም ዘንድ 2/3ኛ ድምጽ የማይገኝበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል፣ በአጠቃላይ ውሳኔውን እንዴት መውሰድ እንደሚቻል ስለሚያስቸግር ህዝቡ ይወስን እስከተባለ ድረስ የህዝቡን ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ አድርጎ መቀበልና የምክር ቤቶቹ ሚና ደግሞ ይህንን የመቀበል /recognition/ ፣ ቢሆንና ቀጥሎም ክልል ለመመሥረት ወዘተ የሚለው በሕገመንግሥቱ

መሠረት በአስተዳደራዊ መንገድ የሚታይ ቢሆን እንደሚሻል አሳስበዋል፡፡

ክቡር አቶ ከማል ማብራሪያቸውን በመቀጠል በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ይሰጥ የሚለው የሕግ ትርጉም የመስጠት ነው ወይስ ሌላ? ተብሎ የቀረበውን በተመለከተም ይህ እንደሁኔታው ሊለያይ እንደሚችል፣ ምክር ቤቱ አንድን መብት ለአንድ አካል ከሰጠ በኃላ በአፈፃፀሙ ላይ ተገቢ የሆነ የጊዜ ገደብ ካላስቀመጠ የክልል ምክር ቤቱ አጠናዋለሁ እያለ እስከ 10 ዓመት ቢያቆየው ተገቢ ስላልሆነ ገደቡ አስፈላጊ መሆኑን፣ ሆኖም የጊዜ ገደቡን የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ በራሱ ነው ወይስ ከክልሎች ጋር በመነጋገር በጋራ በሚደርሱበት ስምምነት መሠረት? የሚለው በሒደት የሚታይ ስለሆነ እንዲሁ ከምንም ተነስቶ ውሳኔው ሕገ መንግስታዊ ነው ወይም አይደለም ማለቱ እንደማያስኬድ፣ በመሆኑም ትርጉም መስጠት የሚያስፈልገው በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠው ባጭሩ ከመሆኑ አኳያ ግልፅ ስላልሆነ ለማብራራት እንደሆነና ይህም ሕግ የማሻሻል ጠባይም እንዳለው፣ ሆኖም አሁን የተሰጠው ትርጉም ራሱ ዘላለማዊ ሳይሆን ወደፊት እንደሁኔታው የተለየ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል መሆኑን ተገንዝቦ ለመነሻነት የሚሆን ሊያስኬድ የሚችል ነገር ከቀረበ ተቀብሎ መሔዱ እንደሚጠቅም ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም ክብርት አፈ ጉባኤዋ ክልሉ የሚወስንበት ጊዜ ቢዘገይ ከአንድ ዓመት እንዳይበልጥ ጥያቄውን ማቅረብ ያለበት

ማነው? የሚለው ግን በሒደት የሚታወቅ መሆን እንዳለበት፣ በምን ዓይነት አግባብ የሚለውም የመጨረሻው ሕዝበ ውሳኔ መሆኑን ማለትም ሕገመንግስቱን ከማስጠበት አኳያ የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤት ግልፅ አካሄድ ካስቀመጡ በኃላ በተቀመጠው አካሄድ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪው አካል ሕዝብ መሆኑን፣ እነዚህን በመከተል እየሰሩ በቀጣይ ደግሞ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሻሉ ግልፅ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ እንጥራለን የሚል አስተያየት መቅረቡን አውስተው ይህንን የሚቃረን ሃሳብ ካለ እንዲቀርብ መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

በዚህም መሠረት ክቡር አቶ ፀጋዬ ማሞ በሰጡት አስተያየት ከላይ በቀረቡት በሁሉም ላይ እንደሚስማሙና የስልጤ ጉዳይ ቀደም ሲልም ሲታይ የቆየ በመሆኑ ቢዘገይ በአንድ ዓመት ውስጥ እንዲወሰን የሚለውን እንደሚቀበሉት ገልፀው ይህ የጊዜ ገደብ ለሁሉም ይሥራ ከተባለ ግን አንድ ዓመቱ አጭር ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር እንደማይስማሙበት ጠቁመዋል፡፡

ይህንን ሲያብራሩም የህዝብ መብት በማንኛውም መንገድ መከበር ያለበት ስለ መሆኑ የማይስማማ አካል ባይኖርም ጥያቄውን ማን ያንሳው? በምን አካሄድ ይፈፀም? በሚሉትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ እርግጠኛ ባልተሆነበት ሁኔታ ግን እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች በተነሱ ጊዜ ሁሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መወሰን አለባቸው ብሎ ማስቀመጡ አስቸጋሪ እንደሚሆን በመሆኑም

በሕዝብ መብት ስም የሚነሱ ጥያቄዎች የሕዝብን መብት ሲሸራርፉ የሚገኙበት ሁኔታም ስለሚኖር ለስልጤ የተከተልነው አሠራር ለሁሉም ይሥራ ማለቱን እንደማይቀበሉት ገልፀዋል፡፡

በመቀጠል ደግሞ ክቡር አቶ አለማየሁ ዓለሙ የተጠቀሰውንና መሰል ጉዳዮችን እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል በሕገመንግስቱ በግልፅ ባልተሸፈነበትና በቀጣይ ውይይት በማድረግ ማዳበርና ማስቀመጥ አስፈላጊ እንደሆነ ቤቱ በተገነዘበበት ሁኔታ ከጉዳዩ አንጻን ነጥብ ማለትም ጊዜዋን ብቻ አንስቶ አካሄድ ማስቀመጥ ጠቃሚ እንደማይመስላቸው ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል ክልሉ ራሱ የጊዜ ገደብ ካልተቀመጠለት ዋጋ ሰጥቶ ባፋጣኝ አይሠራም የሚል እምነት እንደሌላቸው፣ ከዚህ አኳያ የስልጤ ጥያቄ እንደቀረበ ክልሉ ወዲያውኑ ወደ ሕዝቡ በመሄድ ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት መሞከሩን፣ ሆኖም ክልሉ የተከተለው አካሄድና የተደረሰበት ውሳኔ አጥጋቢ አይደለም የሚሉ ጥያቄውን ያቀረበው ማህበረሰብ አባላት እስካሉ ድረስ ጉዳዩ ደግሞ ሊታይ እንደሚገባ ምክር ቤቱ ተገንዝቦ መወያየቱን ካወሱ በኋላ ይህ በሆነበት ሁኔታ በሁሉም እንዲሠራ አንድ ዓመት የጊዜ ገደብ አስቀምጦ ማለፉን እንደማይደግፉት ገልፀዋል፡፡

ክቡር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ በበኩላቸው ምክር ቤቱ ካካሄደው ውይይት የአንድን ብሔረሰብ ማንነት መወሰን ያለበት ማነው ለሚለው ምላሽ ማግኘታቸውን፣ የሚወስንበትን ሥርዓት በተመለከተም እያንዳንዱ ሰው መወሰን እንዳለበት እንደሚያምኑ

ገልፀው ከዚያ ውጭ ግን የአፈፃፀም ሥርዓቱን አሁን ለማስቀመጥ የበሰለ ጉዳይ እንደሌለ፣ እነዚህ ያልበሰሉ ጉዳዮች በቀጣይ በሚካሄዱ ውይይቶችና ወርክሾፖች ዳብረው ውሳኔው መወሰን እንዳለበት እምነታቸው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ቀጥለውም አንድ ክልል እሆናለሁ ለሚል የጊዜ ገደቦችና የአካሄድ ሥነ ሥርዓቶች እነደተቀመጡ ሁሉ ለማንነት ጥያቄም ቢሆን መቀመጥ እንዳለበት፣ በመሆኑም እነዚህ ጉዳዮች ሁሉ ባልተመለሱበት ሁኔታ የጊዜ ገደብ አስቀምጦ መሔድን እንደማይቀበሉት ገልፀዋል፡፡

በተለይ የስልጤን ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ ጥያቄው ቀደም ሲል ተነስቶ ክልሉም ብዙ የሰራበት በመሆኑ አሁንም መታየት እንዳለበትና ወደክልሉም መላክ እንደሚችል፣ ክልሉም ጉዳዩን ለመፍታት ዝግጁ እንደሆነ፣ በመሆኑም ለስልጤ ብቻ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጥ ብሎ ማስቀመጡ የሚያስኬድ ሲሆን ለሁሉም ይስራ ለማለት ግልጽ የሆነ ነገር አሁን እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡

ክቡር አቶ ሀሰን ሺፋ በበኩላቸው የስልጤን ጉዳይ በሚመለከት ክልሉም ብዙ የሰራበት በመሆኑ ለእሱ እልባት መስጠቱ ተገቢ መሆኑንና የማንነትን ጥያቄ ማነው የሚያቀርበው በሚለው ላይ ተወያይቶ አንድ አይነት ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል የሁሉም ጉዳይ በስልጤ መንገድ ይሒድ ማለቱ ግን አከራካሪ እንደሆነና ጉዳዩም እንዲህ በቀላሉ የሚታይ ስላልሆነ ወደፊት በውይይት አዳብሮ ክልል እንደመመስረት ወይም እንደ ሌሎች ጥያቄዎቸ ሁሉ ለማንነት ጥያቄም አንድ አይነት አካሄድ ማስቀመጡ እንደሚጠቅም ገልፀው በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ይፈጸም የሚለውን የስልጤን ጉዳይ ብቻ ለመፍታት መጠቀሙ እንደሚሻል አስገንዝበዋል፡፡

ከዚያም ክብርት አፈ ጉባኤዋ በጉዳዩ ላይ በቂ ውይይት የተካሄደበት ስለሆነ በድምጽ ወስኖ ማለፍ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው በቅድሚያም የጊዜ ገደብን ጨምሮ ማን ይወስናል፣ በምን ስርአት ይወስናል፣ ማን ያቀርባል የሚለውን በተመለከተ ቤቱ ቀደም ሲል የወሰነው ማለትም ለሁሉም ሊያስኬድ ይችላል በሚለው ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ጠይቀው 32 የድጋፍ ድምጽ የተመዘገበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ግን የተቀረው እንዳለ ሆኖ የጊዜ ገደብ መቀመጥ የለበትም በሚል 23 የተቃውሞ ድምጽ ሲመዘገብ ያለምንም ድምጽ ተአቅቦ የመጀመሪያው ሃሳብ በአብላጫ ድምጽ አልፏል፡፡

በዚህ ጊዜም ክብርት አፈ ጉባኤዋ የዴሞክሲያዊ አሰራርን በመከተል የአብላጫውን ድምጽ ውሳኔ ቤቱ በመቀበል ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ መኖር እንዳለበት ቢያስቀምጡም ሁኔታው ግን በሂደት ታይቶ ወርክሾፖችና ሌሎች ጥረቶች

ከተደረጉ በኃላ ሊሻሻል የሚችል መሆኑን መታወቅ እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

ቀጥለውም የስልጤ ጉዳይ በምን መልክ ይታይ በሚለው ላይ ውይይት እንዲካሄድና እንዲወሰን መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

በዚህም መሰረት ክቡር አቶ ሀሰን ኢብራሂም በሰጡት አስተያየት የስልጤ ጉዳይ ቀደም ብሎ የቀረበና ለብዙ አመታት ሲንከባለል የቆየ ክልሉም የሚያውቀው ጉዳይ ስለሆነ የጊዜ ገደቡ አጠር ይበል ከሚባል በቀር በተቀመጠው አካሄድ መሰረት ቢኬድበት ተገቢ እንደሆነ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

ክቡር አቶ አህመድ ሰይድ በበኩላቸው ክልሉ ራሱ ሃላፊነት ያለበትና ጉዳዩንም በአጭር ጊዜ እልባት ሊሰጠው የሚፈልግ ስለሆነ በአጠቃላይ የተቀመጠው የአንድ አመት የጊዜ ገደብ እንዳለ ቢሆንም ክልሉ ከፈለገ ግን በአንድ ወርም ሆነ በፈለገ ጊዜ እንዲጨርሰው መተው የተሸለ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከዚያም ክብርት አፈ ጉባኤዋ የተለየ ሃሳብ ካለ እንዲቀርብ ጠይቀው ባለመቅረቡ ቀደም ሲል ለአጠቃላዩ በተቀመጠው አካሄድ መሰረት የስልጤ የማንነት ጥያቄም ወደክልሉ ተመልሶ እንዲታይ፣ ክልሉ መልሶ ይየው ሲባልም የተቀመጡትን አቅጣጫዎች ተከትሎ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪው አካል ራሱ ህዝቡ እንደሆነ ቤቱ መወሰኑንና በዚህ ውሳኔ ላይም በአባላት መካከል ልዩነት እንደማይታይ ጠቁመዋል፡፡

አያይዘውም ሕዝቡ ራሱ እንዲወስን እያንዳንዱ ሰው ቀርቦ ለማንነቱ ሃሳቡን በምስጢር ድምጽ የሚሰጥበት፣ ሌሎች አካላትም ነፃ ሆነው ሒደቱን የሚታዘቡበትን አግባብ ይመቻቻል የሚለውም አብሮ መታየቱንና በዚህም ላይ በፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ዘንድ ልዩነት እንዳልታየ አመልክተዋል፡፡

የማንነትን ጥያቄ ማን ያቀርባል የሚለውን በተመለከተም ጥያቄውን ማንም ሊያቀርብ እንደሚችል ሆኖም ጥያቄው ትክክለኛ የሕዝብ ጥያቄ መሆን አለመሆኑ በሒደት በሚሰሩ ስራዎች የሚወሰኑ፣ የሚነጥሩና የሚለዩ መሆናቸውን፣ የማንንት ጥያቄ ውሳኔ የሚገኝበት ጊዜም ቢበዛ ከአንድ አመት እንዳማይበልጥና የስልጤ ጥያቄም በዚሁ አግባብ መወሰን እንዳለበት ለዚህም ወደክልሉ ተመልሶ ያለፈው አካሄድ ይህንን አካሄድ መሰረት ያደረገ መሆኑ ተፈትሾ የሚደረግ ማስተካከያ ካለ ተደርጎ የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲያገኝ የሚለውን ሃሳብ ቤቱ በ 32 የድጋፍ ድምጽ በ 23 የተቃውሞ ድምጽ መወሰኑን አስታውቀዋል፡፡

ቀጥለውም በጉዳዩ ላይ አስተያየት ካለ እንዲቀርብ በጠየቁት መሰረት ክቡር አቶ ሀሰን ኢብራሂም በሰጡት አስተያየት ቀደም ሲል ቤቱ ድምጽ የሰጠው በአጠቃላዩ ላይ ስለሆነ ለስልጤ ጉዳይ ደግሞ እንደገና ድምጽ መሰጠት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ክቡር አቶ መለሰ ካሜ በበኩላቸው ቀደም ሲል ለአጠቃላዩ ቤቱ ውሳኔ በሰጠው መሰረት የስልጤ ጉዳይም እንዲሔድ ሃሳብ ቀርቦ

የተቃወመው ስሌለ ተመልሶ ድምጽ ሳይሰጥ በዚያው እንዲሄድ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

በዚህ ጊዜም ክቡር አቶ ሀሰን ሺፋ የስልጤን ጉዳይ አስመልክቶ ክልሉ ቀደም ሲል የሄደበት ጉዳይ ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ እንደማይታወቅ፣ የሚታወቅ ነገር ቢኖር ውሳኔው እደተወሰነና ውሳኔው ግን ትክክል አይደለም የሚል ተቃውሞ ከተወሰኑ ክፍሎች መቅረቡ መሆኑን፣ ቤቱም የተነጋገረው አሁን በተቀመጠው አካሄድ መሰረት መሄዱን ክልሉ አረጋግጦ መልስ እንዲሰጠን የሚል መሆኑን መረዳታቸውን ገልጸው ከዚህ አልፎ ስለስልጢ ጉዳይ እንወስን ከተባለ ክልሉን ማስገደድ ስለሚሆን አግባብነት እንደሌለው ጠቁመዋል፡፡

ክቡር አቶ ፀጋዬ ማሞ በበኩላቸው ከስልጤ ጉዳይ በመነሳት ለሌሎችም መፍትሔ የሚሆን አካሄድ ስለተቀመጠ የስልጤንም ለአጠቃላዩ በተቀመጠው አካሄድ መሰረት እንዲፈጸም ማድረግ እንደሚያስፈልግና ስለስልጤ ጉዳይም በተለየ መነጋገር እንደማያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

በሌላም በኩል ክቡር አቶ አለማየሁ አለሙ ከላይ የተቀመጡት አቅጣጫዎችና መነሻ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት የክልል ምክር ቤቶች ራሳቸው ተወያይተው ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጡ ጉዳዩ ይመለስላቸው በሚል ቤቱ የተስማማ እንደሚመስላቸው ጠቁመው ከዚህ ውጭ የስልጤን ጉዳይ ክልሉ

እንደገና ህዝበ ውሳኔ ያሰጥ የሚባል ከሆነ ግን ነገሩ ግልጽ እንዳልሆነላቸው ጠቁመዋል፡፡

በዚህ ጊዜም ክቡር አቶ አብዱልዋሲዕ ዩሱፍ ቀደም ሲል ክብርት አፈ ጉባኤዋ አጠቃለው ባስቀመጧቸው ጉዳዮች ላይ ቤቱ ከስምምነት ላይ መድረሱንና የስልጤን ጉዳይ በተመለከተም ክልሉ ከአሁን በፊት የጀመረው ስራ ስላለ አንድ አመት ጊዜውን ሳይጠብቅ በሶስት ወር ጊዜም ሊጨርሰው ይችላል የሚል አስተያየት ከደቡብ ክልል ተወካይ መቅረቡን አውስተው በተቀመጠው አካሄድ መሰረት የስልጤም ጉዳይ እንዲወሰን አስተያየት አስቀምጦ ከማለፍ በቀር ስለስልጤ ጉዳይ በተለይ ለመወያየት ግን ኢንፎርሜሽንም በበቂ ሁኔታ ስለሌለ ውሳኔው እንደማያስኬድ ጠቁመዋል፡፡

ክብርት አፈ ጉባኤዋ በበኩላቸው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጤንና ክልል ምክር ቤቱን አቅርቦ ለማከራከር ፍላጎትም እንደሌለውና ዓላማውም ሆነ ሀላፊነቱም እንዳልሆነ፣ በመሆኑም ቀደም ሲል በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ለሁሉም በአጠቃላይ የሚሠራ አካሄድ መከተል ይገባል የሚለውን ቤቱ መቀበሉን አውስተው ትክክለኛው አካሄድም ይኸው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀመንበር በበኩላቸው የምክር ቤት አባል ስላልሆኑ ስለሚወሰነው ጉዳይ ሃሳብ መስጠት ባይችሉም የግል አስተያየታቸውን ለመስጠት ግን እንደሚፈልጉ ጠይቀው ስለተፈቀደላቸው በሰጡት አስተያየት ከስልጤ ጉዳይ

በመነሳት አጠቃላይ የአሰራር ስልት ከተቀመጠ የስልጧውንም በዚሁ ሁኔታ እንዲታይ ወስኖ ማለፍ እንደሚያስፈልግ፣ ከዚሁ በተጨማሪም ክልሉ ከዚህ ቀደም የተከተለው አሠራር ትክክል ነበር አልነበረም የሚለው አስተያየት ውስጥ ሳይገባ የክልሉን የእስካሁን እንቅስቃሴ በአውንታዊ ጎኑ በማየት አሁን በተቀመጠው አካሄድ መሠረት አይቶ ማስተካከል ካለበትም እንዲያስተካክል ጠቁሞ ማለፉ በቂ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በዚሁ ጊዜም ክቡር አቶ ሀሰን ሺፋ በሰጡት አስተያየት ጉዳዩን በሁለት መልኩ ማየት እንደሚቻል ይኸውም ክልሉ ከዚህ ቀደም የተከተለው አሠራር ትክክል አልነበረምና ይታረም የሚለው የማይኖሪቲው ሃሳብ በአንድ በኩል፣ አጠቃላይ አካሄድ ስለተቀመጠ ክልሉ ከተቀመጠው አካሄድ ጋር ያለፈውን አሠራሩን በማገናዘብ ይሄድበት የሚለው በሌላ በኩል ሊያስኬድ እንደሚችልና ምክር ቤቱ ማድረግ ያለበት ግን በሁለተኛው መንገድ ማለትም አጠቃላይ መርሆውን አስቀምጦ አሠራሩን ለክልሉ መተው ነው ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ክብርት አፈ ጉባኤዋም በጉዳዩ ላይ የተካሔደው ውይይት ከላይ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት መቋጨቱን ከገለፁ በኋላ በዕለቱ በምክር ቤቱ ውይይት በመገኘት ለውይይቱ መሳካት አስተዋፆ ስላደረጉ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀመንበርን አመስግነው የዕለቱ ስብሰባ ከቀኑ 12፡30 ሰዓት ላይ ተጠናቋል፡፡